

በከፋ ሀ/ ስብከት በሊሙ አውራጃ መካነ ጥበብ መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን

ዋጋው አንድ ብር

# ትንሣኤ



የገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን

ቁጥር ፺፬

ሐምሌ ፲፱፻፸፯ ዓ.ም

www.ethiopianorthodox.org

«ይህ መጽሔት የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ፤ሥርዓትና ዜና፤ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ። »


አዘጋጅ
ልሣነወርቅ በዛብኅ ፤
ም/ ከንፈ ርግብ ማርቆስ




በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ በወር አንድ ጊዜ እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 110754
የመልእክት ሣ. ቁ. 3137
አዲስ አበባ ፤


# ማውጫ

**አርእስት** **ገጽ**


ደብዳቤዎች ........................ ፩
ዘመነ ክርም ........................ ፪
ምሥጢረ ሥላሴ ........................ ፬
እንግዶችን መቀበል አትርሱ ........................ ፮
የቤተ ሰብ አመሠራረትና መዋቅር ........................ ፰
በሬና ገበሬ ዘርና መሬት ........................ ፱
ዜና ሊቃውንት ........................ ፲
ጻድቁ አባ ሊባኖስ ........................ ፲፪
ፀባቲ ገብረ ሥላሴ ወንድም አገኘሁ ........................ ፲፬
ጴጥሮስ ወጳውሎስ ........................ ፲፭
ሕሙማንን ሁሉ እንዲፈውሱ ሥልጣንን ሰጣቸው ........................ ፲፯
ልማት በቤተ ክርስቲያን ........................ ፲፰
ዜና ዕረፍት ........................ ፲፱
የግብርና በረከት ........................ ፳፩
ልብሰ ክህናት ........................ ፳፪
የወባ በሽታ ........................ ፳፫
የአለን ቅዱስ ጊዮርጊስ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ተፈጸመ ........................ ፳፬


በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ የስነ ጽሑፍ አዘጋጅ ክፍል የፖ.ሣ.ቁ. 3137
አዲስ አበባ ፤

በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሃዱ አምላክ አሜን ።

በመጀመሪያ በጌታችን በመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱንም በድንግልና በወለደችው በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የክብር ሰላምታችንን እያቀረብን ለምናቀርብላችሁ መንፈሳዊያን ጥያቄዎች የሚያረካ መልስ እንደምትሰጡን እንተማመናለን ።

፩ኛ/ በወንጌል ያላመነ ያልተጠመቀ አይድንም ይላል ነገር ግን ክርስትና ሳይነሱ የሚሞቱ ሕፃናት ለጥምቀት ስላልበቁ አይድኑም ማለት ነውን ? ወይስ እንዴት ነው ? ።

፪ኛ/ ዐቢይ ጾም ፵ ጾም በመባል ይጠራል ይኸውም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የጾመው ፵ ቀን መሆኑ ነው ነገር ግን ይህ ጾም በሀገራችን ሁለት ወር ይጾማል ለምን ፳ ቀን ተጨመረ ?

፫ኛ/ አንዳንድ ደብተሮች ኮከብ እንቆጥራለን እያሉ የሰዎችን ውስጣዊ ጠባይንና የወደፊት አላማ እናውቃለን እያሉ ይተነብያሉ ዓውደ ነገሥት የሚባል መጽሐፍንም ይመለከታሉ ይህ ነገር ምን ያህል እውነተኛነት አለው ።

፬ኛ/ በአንዳንድ አብያተ ቤተ ክርስቲያናት በስዕሉ ጥግ የሻማ መብራት ይበራል እንደዚሁም በአንዳንድ ቤቶች የማርያምንና የሚካኤልን የመሳሰሉትን ማኅበር ሲያከብሩ በስዕሎች አካባቢ መብራት ያበራሉ ይህ ነገር በልምድ ነው ወይስ በመጽሐፍ ይገኛል ?
የእግዚአብሔር ቸርነት ከሁላችን ጋር ይሁን አሜን

ከተማሪ ግዛው ዓለማየሁ ።
ከብሥራተ ቅዱስ ገብርኤል የሰንበት ት/ቤት ባሕር ዳር ጐጃም

ተማሪ ግዛው ዓለማየሁ በየወሩ እየታተመ የሚወጣውን የትንሣኤን መጽሔት ተመልክተህና ጠቃሚነቱንም ተገንዝበህ አስተያየትን ስላቀረብክልን እናመሰግንሃለን ፤ ስላቀረብካቸውም ጥያቄዎች መልሱ እንሆ ፤

፩ኛ ጥያቄ ወንድ ልጅ ፵ ቀን ሴት ልጅ ፹ ቀን ሳይሞላቸው በድንገት ቢሞቱና ሳይጠመቁ በሞት ቢለዩ የምእመናን ርስትና ጉልት ገነት መንግሥተ ሰማያት ናትና ወደርስታቸው ይገባሉ እንጂ ኩነኔ የለባቸውም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያላመነ ያልተጠመቀ ይኰነናል ያለው ተምረው ትምህርቱን ያልተቀበሉትን ነው እንጂ ፵ ቀን ወይም ፹ ቀን ስላልሞላቸው የምእመናን ልጆች አይደለም ።

፪ኛ/ ጥያቄ ዓቢይ ጾም ፵ ጾም ተብሎ መጠራቱ ግልጽ ነው ። ይኸውም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የጾመው ፵ ቀን ስለሆነ ነው ማቴ ፬ ፡ ፩ ።

ነገር ግን ለምን እኛ ፪ ወር እንጾማለን ስላልከው ተሳስተሃል እኛ የምንጾመው ፶፭ ቀን ነው ። በዓቢይ ጾም መግቢያ ያለው አንድ ሳምንት ጾም ጾመ ሕርቃል ይባላል ይኸውም ያለምክንያት አይደለም በኢየሩሳሌም ፎቃ በሮም ሕርቃል የሚባሉ ነገሥታት ነግሠው ነበር በኢየሩሳሌም ነግሦ የነበረው ፎቃ የተሰኘው ንጉሥ ምእመናኑን ስላሰቃያቸውና መግቢያና መውጫ ስላሳጣቸው እገዘን ይህንን ፎቃ የተባለውን ንጉሥ አጥፋልን ብለው ወደ ሮሙ ንጉሥ ወደ ሕርቃል ላኩ እሱም ሐዋርያት ነፍስን የገደለ መላ ሕይወቱን ይጹም ብለው ሥርዓት ሠርተዋል ። ስለዚህ አይቻለኝም አላቸው እነሱም እሱን አጥፋልን ከደረሰብንም ችግር አላቅቀን እንጂ እኛ እንጾምልሃለን ። አሉት ። በዚህ ጊዜ እንዲህ ከሆነስ መልካም ነው በማለት ጥያቄያቸውን ተቀብሎ መጥቶ ፎቃ የተባለውን ጠላታቸውን አጥፍቶ ስለ ተመለሰ ለሕርቃል ሲባል የተጀመረ ጾም ነው ። ኋላ ግን የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ጾም የሚጠቅም እንጂ የሚያስጐዳ አለመሆኑን ተገንዝበው በዓቢይ ጾም መግቢያ እንዲጾም ስለ ወሰኑ እንጾመዋለን ።

በመጨረሻ ያለውም ሰሙነ ሕማማት ይባላል ። ይህንንም ጾም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ሰው ልጅ ሲል የተቀበለውን ጸዋትወ መከራ ለማስታወስ የምንጾመው ጾም ነው ።

ስለዚህ በመግቢያ ያለው አንድ ሳምንትና በመጨረሻ ያለው አንድ ሳምንት ጌታ ከጾመው ከ፵ ቀን ጋር ተደምረው ፶፭ ቀን እንጾማለን እንጂ ጌታ የጾመውስ ልክ ፵ ቀን ብቻ ነው ።

፫ኛ/ ጥያቄ እንደ እነዚህ የመሳሰሉት ጠንቋዮች የሰው ልጅ በደከመበትና ወዙን አንጠፍጥፎ ያፈራውን ሀብት ለመዝረፍ በማያገባቸው ነገር እየገቡ የሰውን ገንዘብ ሲዘርፉ ይኖራሉ እንጂ እውነት አዋቂዎች ሁነው አይደሉም እውቀትማ ቢኖራቸው ለራሳቸው አያውቁም ነበርን ? የዋሆች ከሆኑ ሰዎች ሳንቲሞችን ሲዘርፉ ሰዎችን ሲያታልሉ የሚኖሩ አታላዮች ናቸው እንጂ አንዲት ዕውቀት እንደ ሌላቸው እነሱን አይተህ ልትረዳ ትችላለህ የጠንቋይ ድኃ እንጂ የጠንቋይ ሀብታም የለም እንዲሁ የጠንቋይ በሽተኛ እንጂ የጠንቋይ ጤነኛ የለም ። ጠንቋዮች ሥር እየማሱ ቅጠሉቹንም እየበጠሱ በሽተኞችን እናድናለን የሚሉ በጥቂቱ የሚገመቱ አይደሉም ነገር ግን በጠንቋዮች የተጎዱ እንጂ በጠንቋዮች የተጠቀሙ በሽተኞች ፈጽሞ አይገኙም ። ስለዚህ ባጭሩ የሚጠነቁልም ሆነ የሚያስጠነቁል ሁለቱም የእግዚአብሔር ጠላቶች ናቸው በጠንቋይ የተዋረደ እንጂ በጠንቋይ የከበረ የለም ።

፬ኛ/ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚገኙት ስዕሎች አካባቢ ሻማ ያበራሉ እንደዚሁም እያንዳንዱ ግለሰብ የጻድቃንን የሰማዕታትን የእመቤታችን ቅድስት

ወደ ገጽ ፯ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

## ርእሰ አንቀጽ

# ዘመነ ክርም

በቤተ ክርስቲያናችን ሲነገር በመጣው መሠረት ዓመቱ በአራት ክፍሎች ይከፈላል አንደኛ ከመስከረም ፳፭ እስከ ታህሣሥ ፳፭ ያለው ነው ይህም ዘመነ መፀው ይባላል ሁለተኛው ከታኅሣሥ ፳፭ እስከ መጋቢት ፳፭ ያለው ዘመነ ኀጋይ ተብሎ ይጠራል ከመጋቢት ፳፭ እስከ ሰኔ ፳፭ ቀን ዘመነ ፀደይ ተብሎ ሲሠየም ከሰኔ ፳፭ እስከ መስከረም ፳፭ ቀን ያለው ዘመነ ክርም ተብሎ ይጠራል ።

በዚህ ጽሑፍ የአራቱንም ዘመናት ሁኔታ ዘርዝሮ ለማስረዳት ሳይሆን ስለ ዘመነ ክርም ይዞታ በአጭር ለመግለጽ ነው የክረምቱ ወራት ሦስት መሆናቸው የታወቀ ነው በእነዚህ ወራት ዝናማት ይዘንማሉ አፍላጋት ከአፍ እስከደገፋቸው መልተው ይፈሳሉ መባርቅት ይበርቃሉ ነጕድጓድ ይነጕዳል አዝርእት ይበቅላሉ አትክልት ይጸድቃሉ ዛፎች ይለመልማሉ ሳር ነጭተው ቅጠል በጥሰው ጥሩ ውሀ ተጕንጭተው የሚኖሩ እንስሳት ይጠግባሉ መሬት በጠቅላላ በአረንጓዴ ቅጠል ትሸፈናለች ።

በዚህ ወቅት ገበሬዎች ቀን በእርሻ በቁፋሮ ተጠምደው ሲውሉ ሌሊት ስለሥራቸው ይዞታ ሲያወጡና ሲያ ወርዱ ያድራሉ በወርኃ ክረምት ከላይ ዝናሙን ከታች ጕርፉንና ጭቃውን ሳይፈሩና ሳይሰቀቁ የሚሠሩ ሠራተኞች ተስፋ የሚያደርጉት በመከር ወራት የሚገኘውን የምድር ፍሬን ነው ።

ሐዋርያው ጳውሎስ "ምድር ለደከመላት ሠራተኛ የምትሠጠውን በረከት ሲገልጽ" ብዙ ጊዜ በእርሷ ላይ የሚወርደውን ዝናም የምትጠጣ መሬት ለሚያርሱአትም ደግሞ የሚጠቅሙ አትክልትን የምታበቅል ከእግዚአብሔር በረከትን ታገኛለችና እሾህንና አሚከላን ብታበቅል ግን የተጠላች ናት ለመርገምም ትቀርባለች መ ጨረሻም በእሳት መቃጠል ነው" ሲል ተናግሯል ዕብ ፮. ፯ ።

በሬና ገበሬ መሬትና ዘር በአንድነት የሚስማሙበት ወቅት ይህ ዘመነ ክርም ነው ፣ ገበሬው በሬዎችን ጠምዶ በበጋ ወራት አርሶ ያለሰለሰውን ማሣ የሚዘራው በክረምት ወራት ነው ከልምላሜ ተራቁታ የነበረችው መሬትም ግማሽ አካሏ በልምላሜና በቅጠል ግማሽ አካሏ ደግሞ በእህል ቡቃያ ተሸፍና የሚታየው በወርኃ ክረምት ነው ።

ገበሬው እግዚአብሔርን አምኖ ዋስና ሐላፊ ሳይጠይቅ የተበጠረውንና የተንጠረጠረውን ዘሩን ከጕታ ከጕተራና ከዕሪቅ አውጥቶ በመሬት ላይ ይበትናል መሬትም የገበሬውን አደራ ተቀብላ ዘሩን ቆርጥማ ገበሬውን መና አትሰደውም አንዱን ቅንጣት ፴ ቅንጣት ስሳ ቅንጣት መቶ ቅንጣት በማድረግ መልሳ ታስረክበዋለች ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውን ሥጋ ለብሶ ከተወለደ በኋላ ያስተምርበት በነበረው ወቅት በምሳሌ ሲገልጽ "እነሆ ገበሬ ዘር ሊዘራ ወጣ በእጁ■ ታፍኖ ሲዘራ አንዳንዱ በመንገድ ዳር ወደቀ ወፎችም መጥተው በሉት ሌላውም ብዙ መሬት በሌለበት በጭንጫ ላይ ወደቀ ጥልቅ መሬትም ስላልነበረው በቀለና ፀሐይ በወጣ ጊዜ ጠወለገ ፣ ሥርም ስላልነበረው ደረቀ ሌላውበእሾህ መካከል ወደቀ እሾህም መጣና አነቀው ሌላውም በመልካም መሬት ላይ ወደቀ አንዱም መቶ አንዱም ስድሳ ፣ አንዱም ሠላሳ ፍሬን ሰጠ" ብሏል ማቴ. ፲፫. ፫ - ፰ ።

ወንጌላዊው ማርቆስ በጻፈው ወንጌል "በምድር ዘርን እንደሚዘራ ሰው የእግዚአብሔር መንግሥት እንዲህ ናት ሌሊትና ቀን ይተኛል ይነሣልም እርሱም እንዴት እንደሆነ ሳያውቅ ዘሩ ይበቅላል ያድግማል ምድሪቱም አውቃ በመጀመሪያ ቡቃያ ኋላም ዛላ ኋላም በዛላው ፍጹም ሰብልን ታፈራለች" ይላል ማር ፬ ፣ ፳፮ ።

በዘመነ ክርም ያልበቀለ ቡቃያ በዘመነ መፀው ፍሬን ሊሰጥ አይችልም ማንም ሰው ቢሆን የሚሠራውን ሥራ ወቅቱን ጠብቆ ከሥራ የፈለገውን ለማግኘት ይችላል ምንም ሁሉም ሰው ያለ ሥራ ለመኖር ባይችልም በወርኃ ክረምት ሌሊት በሐሳብ ቀን በሥራ የሚደክሙት ገበሬዎች ናቸው በወርኃ ክረምት የደከሙ ያረሱ የቆፈሩ ገበሬዎች በመከር ወራት ድካማቸውን ረስተው በደስታ ይዋጣሉ ዝናቡንና ጭቃውን ፈርተው በስንፍና ያለሥራ የከረሙ ሰዎች ግን በመከር ጊዜ የበይ ተመልካች ይሆናሉ።

ክቡር ዳዊት በመዝሙር ፻፳፭ ቁ. ፭ "በልቅሶ የሚዘሩ በደስታ ይለቅማሉ በሄዱ ጊዜ ዘራቸውን ተሸክመው እያለቀሱ ተሠማሩ በተመለሱ ጊዜ ግን ነዶአቸውን ተሸክመው ደስ እያላቸው ይወጣሉ" ይላል ።



ያለ መከራ ጸጋ አይገኝም እንደሚባለው በክረምት ወራት ዝናሙን ብርዱን ጭቃውን ሳይፈራና ሳይሰቀቅ የሠራ በመከር ወራት ደስታው እጽፍ ድርብ ሲሆን የክረምቱን ብርድና ዝናም ፈርቶ ሳይሠራ ወርኃ ክረምቱን ያሳለፈ ሰነፍ ሰው ግን በመከር ወራት የሚያተርፈው የማይጠቅም ጸጸት ይሆናል ችግርም ይጸናበታል ።

ስለዚህ ወርኃ ክረምቱን በስንፍና አሳልፈው በዘመነ መፀውና በዘመነ ሐጋይ በችግር ላድ እንዳይወድቁ በዚህ ወቅት ነቅተውና ተግተው እንዲሠሩ በግብርና ሙያ ለተሠማሩ ወገኖቻችን መንፈሳዊ መልእክታችን እናስተላልፋለን ።



www.ethiopianorthodox.org

# ምሥጢረ ሥላሴ

ከመምህር ሀብተ ማርያም ተድላ

"ምሥጢር" የሚለውን ቃል በሁለት ዐበይት ክፍሎች ማየት ይቻላል። እነዚህም አንዱ የፈጣሪ ፣ ሁለተኛው የፍጡራን ምሥጢር በማለት አእምሮ እስከ ደረሰበት ድረስ መመልከት ሲቻል ነው ።

የፈጣሪን ምሥጢር ለማየት መግቢያ በሩ መነጽሩ የፍጡራን ስለሚሆን እስቲ አስቀድመን የፍጡራንን ምሥጢር እንመርምር ።

አሁንም የፍጡራንን ምሥጢር በሁለት ክፍሎ መመልከቱ አስፈላጊ ይሆናል ። ይኸውም የመላእክትና የሰው ልጆች ምሥጢር ብለንና ከፍለን ብንመለከተው ቀና መንገድ ይሆንልናል ።

ሀ/ የሰው ልጆች ምሥጢር

ይህ ምሥጢር የሰው ልጆች አንድ ወይም ከአንድ በላይ ሁነው በሥውር ወይም በምሥጢር የሚይዙት ነው ።

የሰው ምሥጢር እንደሁኔታው ሰው አዩኝ አላዩኝ ብለው በድብቅ የሚፈጽመው ተግባር ነው ይህም ለሌሎች ምሥጢር ሁኖባቸው ላልተወሰነ ጊዜ ይኖራል ።

ለ/ የመላእክት ምሥጢር

የመላእክት ተፈጥሮ ራሱ ምሥጢር ነው ለማለት ይቻላል ። መላእክት የተፈጠሩት ከነፋስ ፣ ከእሳት ነው ፣ ወሶበ ኢያእኰትኮ ለዘፈጠረከ እምነፋስ ወነድ ፈጠረ ሀየንቴከ ሰብአ ዘማሬ" ከነፋስና ከእሳት የፈጠረህን (አምላክ) ባታመሰግነው ባንተ ፈንታ አመስጋኙን ሰውን ፈጠረ ተብሎ ተጽፏልና ፣ መቅድመ ወንጌል ።

የመላእክት መልካቸውን ቅርጻቸውን ቁመታቸውን የሚያውቅ ስለሌለ ለሰው ልጆች ከባድ ምሥጢር ሁኖ ይኖራል የተባዕታይና የእንስታይም ጾታ በመላእክት ተፈጥሮ እንደሌለ የታመነ ነው ። (ቢሆንም ለሰው በዘፈቀደ በሚገለጹበት ጊዜ በተባእታይ ጾታ እንጂ በአንስታይ ጾታ ተገልጸው አልታዩም ።)

መላእክት ለቀደሙት አበው ነቢያት ለሐዋርያትና ለበቁት ሊቃውንት በልዩ ልዩ አምሳል ተገልጸውላቸዋል በሰው አምሳል የተገለጹላቸው አሉ ፣ በተለያየ የእንስሳት አርአያ የተገለጹላቸው አሉ ፣ ክንፋቸውን ዘርግተው እንደ አሞራ ሲበሩ የታዩበት ጊዜ አለ ሁኔታቸው አስደናቂ ቢሆንም የፈጣሪን ከሃሊነት የሚያንጸባርቅ እንጂ በራሳቸው ችሎታ ባለመሆኑ የሚያስደንቀው ያው የፈጣሪን ጥበብ ነው ። የመላእክት ተፈጥሮ አስደናቂ ምሥጢር ነው ብንልም ለዚህ ምሥጢር ባለቤት ፈጣሪ ስለሆነ እናደንቀዋለን እናመሰግነውማለን ። ነገር ግን የእግዚአብሔር ምሥጢር ከዚህ ሁሉ የተለየ ነው ፣ ባሕርየ እግዚአብሔር ራሱ ትልቅ ምሥጢር ነውና ዓለማት ከየት መጡ ? ማንስ አመጣቸው ? የሚል ጥያቄ የዘመናችን የፊደል መቁጠሪያ ሁኗል ቢባል ከእውነት አይርቅም ። ሌሎችም ያልታወቀ ታላቅ ኃይል አለ ይላሉ ፣ ክርስቲያኖችና ሌሎችም አማንያን እግዚአብሔር በማይታወቅ ረቂቅ ጥበብ እምኀበ አልቦ አመጣው በማለት ያምናሉ ።

ዓለማት ሳይፈጠሩ እግዚአብሔር ራሱ የት ነበር ? ምንስ ይሠራ ነበር ? እሱ ራሱ ከምን ተገኘ ? የሚሉ ጥያቄዎችም በአንዳንዶች ሕሊና መጉላላታቸውና አንዳንድ ጊዜም መጠየቃቸው አልቀረም ። ነገር ግን የፈጣሪን ምሥጢራዊ ባሕርይ መርምሬ አገኘለሁ ብሎ መድከም የዋህነት ይሆናል ። ለምሳሌ አንድ ሠዓሊ ጥሩ ሥዕል በድንጋይ ሠሌዳ ቀርጾ ቢያስቀምጥ ራሱ ሠዓሊው እኔ እገሌ በእንዲህ ያለ ጊዜ ተወለድሁ በእንዲህ ያለ ዘመን ይህንን ሥዕል ሣልሁ ብሎ ካልመዘገበ በቀር ሥዕሉ (ቅርጹ) "እኔን የሠራ እገሌ በእንዲህ ያለ ቦታ በእንዲህ ያለ ዘመን ተወለደ...። ብሎ የሠሪውን ታሪክ መናገር አይችልም።ስለዚህ የእግዚአብሔርን ምሥጢር ማወቅ የሚችለው ራሱ ባሕርየ እግዚአብሔር ብቻ መሆኑ መታወቅ ይኖርበታል ። ማንም ይሁን ማን የእግዚአብሔርን ባሕርይ መርምሮ ማወቅ ስለማይችል ከፍጡራን ሕሊና ሁሉ ምሥጢር ሁኖ ይኖራል ። ቢሆንም ጠቢበ ጠቢባን እግዚአብሔር ሰውን ከመውደዱ የተነሣ በመጠኑም ቢሆን ምሥጢሩን በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ (በልጁ) አማካይነት ከዚያም በተከታዮቹ በሐዋርያት የገለጸልን ስለሆነ ዐቅማችን እስከፈቀደልን ድረስ ለመመርመር እንሞክር ።

"ምሥጢረ ሥላሴ"

በዘመነ ብሉይ የአንድነትና የሦስትነት ምሥጢር ሳይገለጽ አንድ እግዚአብሔር ተብሎ ይመለክ ነበር እግዚአብሔር የሚለው ስም የአንድነትንና የሦስትነትን ስም የሚያጠቃልል ነው ። ይህም በከንቱ የተነገረ ሳይሆን የቅዱስ መጽሐፍን መልእክት መሠረት በማድረግ ነው ።

ቅዱስ መጽሐፍ እንዲህ ይላል ። ይቤ እግዚአብሔር ንግበር ሰብአ በአርአያነ ወበአምሳሊነ" (እግዚአብሔር አለ ሰውን በመልካችንና በምሳሌያችን እንፍጠር ።

እንግዲህ "እግዚአብሔር አለ" የሚለው ቃል ነጠላ ግሥ ስለሆነ አንድነትን ሲያመለክት ሰውን በመልካችንና በምሳሌያችን እንፍጠር የሚለው ዐረፍተ ነገር ደግሞ ሦስትነትን ያሳያል ። ይኸውም አብ የልብ ወልድ የቃል ፣ መንፈስ ቅዱስ የእስትንፋስ ምሳሌ በመሆን የሚያስብና የሚመራመር ልብ ያለው የሚናገር ቃልና የሚተነፍስ የሕይወት እስትንፋስ ያለው ሰውን እንፍጠር ማለታቸው ነው ።

ሰው በአርአያ እግዚአብሔር ተፈጠረ ሲባል አስተዋይነቱና በጥበብ መሥራቱ ፣ የሚያስብ ልብ የሚናገር ቃልና የሚተነፍስ የሕይወት እስትንፋስ ስላለው ነው እንጂ እግዚአብሔር አጭር ቁመትና ጠባብ ደረት የሚታይበት ውሱን ሁኖ አይደለም ።

፪/ አዳም በምክረ ከይሲ እንዳይበላ የተከለከለውን ፍሬ ዕፅ በበላ ጊዜ እግዚአብሔር አምላክ "እነሆ አዳም መልካምንና ክፉን በማወቅ ከእኛ እንደአንዱ ሆነ" ። አለ ዘፍ.፫ ፣ ፳፪ ።

ከእኛ እንደ አንዱ ማለቱ ከሦስቱ አካላት እንደአንዱ እግዚአብሔር ቃል ሆነ ማለቱን ያሳያል ፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር ቃል በገዛ ፈቃዱ የአዳምን ሥጋ ለብሶ ፣ በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ በዚህ ዓለም ተገልጧልና ።

፫/ ይቤ እግዚአብሔር "ንዑ ንከአው ነገሮሙ ለከለዳውያን ፣ በሰናአር ሜዳ ላይ ግንብ እየሠሩ ሊፈታተኑት የሞከሩትን የኖኅ ልጆች ለመበታተን በፈለገ ጌዜም (ኑ እንውረድና የከለዳውያንን ቋንቋ እንበታትን) አለ ። ዘፍ. ፲፩ ፣ ፮-፲ ። ይህም ዐረፍተ ነገር አንድነትንና ሦስትነትን ያመለክታል ። ኑ የሚለው ቃል ከአንድ በላይ መሆኑን (ይኸውም ሦስትነትን) ሲያመለክት እግዚአብሔር አለ የሚለው አረፍተ ነገር ደግሞ አንድነትን ያሳያል ።

፬ አብርሃም በድንኳኑ ደጃፍ ተቀምጦ ሳለ እግዚአብሔር በመምሬ ዛፍ ሥር ተገለጠለት ዐይኑንም አነሣና እነሆ ሦስት ሰዎች በፊቱ አየ ። ባያቸውም ጊዜ ሊቀበላቸው ከድንኳኑ ደጃፍ ተነሥቶሮጠ ። ወደምድርም ሰገደ እንዲህም አለ አቤቱ በፊትህ ሞገስ አግኝቼ ከሆነ ባርያህን አትለፈኝ ብዬ እለምናለሁ።ጥቂት ውሀ ይምጣላችሁ እግራችሁን ታጠቡ ከዚህችም ዛፍ ዕረፉ።ቁራሽ እንጀራም ይምጣላችሁ ። ልባችሁንም ደግፉ ። ከዚህም በኋላ ትሔዳላችሁ ስለዚህ ወደባርያችሁ መጥታችኋልና ፣ አለ ፣ እነርሱም እንዳልህ አድርግ አሉት። ከዚህ በኋላ የዛሬ ዓመት እንደ ዛሬው ጊዜ ወዳንተ እመለሳለሁ ፣ ሚስትህ ሣራ ልጅን ታገኛለች" በማለት እግዚአብሔር ለአብርሃም አበሠረው። ዘፍ. ፲፰ ፣ ፩-፲፩ ።

ከታሪኩ መገንዘብ እንደሚቻለው አብርሃም በድንኳን ደጃፍ ተቀምጦ ሳለ ያያቸውና የተቀበላቸው ሦስት ነበሩ በሦስትነታቸውም አነጋግረውታል ፣ እንደገናም የባሬ ዓመት ወዳንተ እመለሳለሁ ሚስትህ ሣራ ወንድ ልጅ ታገኛለች በማለት በአንድ ሰው አርአያ አነጋግሮታል ። ይህ ራሱ አንድነትንና ሦስትነትን ያረጋግጥልናል ።

፭/ ይህ ተስፋ ለጊዜው ስለ ይስሐቅ መወለድ ቢሆንም ፍጻሜው ስለ ክርስቶስ ስለሆነ "በዘርእከ ይትባረኩ ኩሎሙ አሕዘበ ምድር" ተብሎ በተነገረው መሠረት ተስፋውን ለመፈጸም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተወልዶ እንደ ሰዎች ሁሉ በጥቂት ካደገ በኋላ በ፴ ዓመቱ በተጠመቀበት ዕለት እግዚአብሔር አብ በደመና ሁኖ የምወደው ልጄ ይኸ ነውና ስሙት በማለት መስክሯል መንፈስ ቅዱስም በአምሳለ ርግብ ወርዶ በራሱ ላይ ዐርፏል ። በዚህ ጊዜ አንድነት ሦስትነት በግልጽ ታየ ።

፮/ የዓለም መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ በሚያስተምርበት ጊዜ "እኔና አብ አንድ ነን ፣ እኔን ያየ አብን አየ በማለት አንድነታቸውን ሲያስተምር ሦስትነታቸውን ሲገልጽ ደግሞ ወደ ዓለም ዳርቻ ሒዱና አሕዛብን ሁሉ አስተምሩ ፣ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸውም ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው" ብሏል ። ዮሐ. ፲፬ ፣ ፰-፲፪ ። ማቴ ፳፰ ፣ ፲፱ ።

ከላይ ከፍ ብሎ እንደተገለጸው በአበው ነቢያት አንድ እግዚአብሔር ተብሎ የሚታመንበት ቢሆንም እግዚአብሔር ማለት አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ማለት መሆኑን በታላላቅ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ተገልጿል ።

ሊቁ ባስልዮስ ዘአንጾኪያ አንስ ሶበ እቤ እግዚአብሔር እብል በእንተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ (እኔ እግዚአብሔር ብዬ በምናገርበት ጊዜ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ማለቴ ነው ብሎአል ። ሃይ አበ ምዕ. ፺፮-፮ ። (ጎርጎሬዎስ) ነባቤ መለኮት ።

ቅዱስ አትናቴዎስም አምላክ ውእቱ አብ አምላክ ውእቱ ወልድ አምላክ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ ፣ አብ አምላክ ነው ወልድ አምላክ ነው ፣ መንፈስ ቅዱስ አምላክ ነው ብሏል ።

እንግዲህ ስማቸው አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ሁኖ አንድ አምላክ ተብሎ ይታመንባቸዋል በዚህምይመለካሉ ። የአካል ሦስትነታቸውን በአብርሃምና በዮርዳኖስ ፈለግ ተመልክተናል ፣ ስማቸውም በአምላካችን በኢየሱስ ክርስቶስ ነተነግሮናል ። የባሕርይ አንድነታቸውም "አነ ወአብ አሐዱ ንሕነ" (እኔና አብ አንድ ነን ከሚለው መለኮታዊ ቃል ሌላ በአንድ ሰው አካል ውስጥ ልብ ቃል እስትንፋስ እንደመኖራቸው መጠን በያንዳንዱ የሥላሴ አካል ሦስት ልብ ሦስት ቃል ሦስት እስትንፋስ ሳይኖር አብ ልብ ፣ ወልድ ቃል መንፈስ ቅዱስ እስትንፋስ ተብለው የባሕርይ አንድነታቸውን ያረጋግጣሉ ።

በዘመነ ብሉይ እግዚአብሔር አብ ፣ በዘመነ ሥጋዌ ኢየሱስ ክርስቶስ (እግዚአብሔር ወልድ ከዕርገት በኋላ መንፈስ ቅዱስ ወርዶ በቅዱሳን ሐዋርያት ልቡና አድሮ ወንጌል በዓለም እንዲትሰበክ መደረጉን ስንመለከት የስም የግብርና የአካል ሦስትነታቸውንና የባሕርይ አንድነታቸውን እናረጋግጣለን ።

ወንጌላዊ ዮሐንስ በመጀመሪያ ቃል ነበረ ቃልም በእግዚአብሔ ርዘንድ ነበር እግዚአብሔር ቃል ነበረ ። ሁሉም በእርሱ ሆነ ሕይወት ነበረ ሕይወትም የሰው ልጅ ብርሃን ነበር በማለት አንድነታቸውንና ሦስትነታቸውን አስተምሮናል ከዚህ የበለጠ እንድናውቅ የዕውቀት ባለቤት እሱን አምላካችንን በእምነት እንጠይቅ ።





www.ethiopianorthodox.org

# እንግዶችን መቀበል አትርሱ

ዕብራውያን ፲፫ ፡ ፪

እንግዳ መቀበል ከስድስቱ ቃላተ ወንጌል አንዱ ነው ፤ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ሁለተኛ ወደዚህ ዓለም በመጣ ጊዜ እንግዳ ብሆን ተቀብላችሁኛልና ዓለም ሳይፈጠር ወደተዘጋጀው መንግሥተ ሰማያት ግቡ ብሎ እንዲገቡ የሚያደርጋቸው በዚህ ዓለመ ሥጋ ሳሉ እንግዶችን ተቀብለው ያበሉትን ያጠጡትን መሆኑን በቅዱሳት መጻሕፍት ተጽፎ እናገኘዋለን ።

እንግዳ መቀበል ከፍተኛ ዋጋን ከእግዚአብሔር የሚያሰጥ መሆኑ በዘመነ ሐዲስ ብቻ ሳይሆን በዘመነ ብሉይም የተለመደ መንፈሳዊ ተግባር ስለነበር ብዙ ሰዎች ተጠቅመውበታል ከቀደሙ ሰዎች እንግዳን በመቀበል ስሙ እጅግ በጣም የታወቀው አብርሃም ነበር ።

አብርሃም ጭቃ ረግጦ ድንጋይ አለዝቦ እንጨት ጠርቦ የመኖሪያ ቤት ሠርቶ በዚያ አልተቀመጠም ድንኳኑን ከተመሳቀለ ጐዳና ተክሎ የወጣውን የወረደውን ያለፈውን ያገደመውን ሰው ሁሉ በእንግድነት እየተቀበለ እያበላና እያጠጣ አሳድሮ ሲነጋ ወደሚሄድበት ቦታ ሸኝቶ ይሰድ ነበር ።

እንግዳ ሳይመጣ የቀረ እንደሆነ እግዚአብሔር የሰጠኝን ምግብ ያለ እንግዳ እንዴት እመገባለሁ በማለት ሳይበላ ያድር እንደነበር ገድለ አብርሃም በተባለው መጽሐፍ ተጽፎ ይገኛል ። ገድሉ በዚህ ቃል ብቻ ሳይወሰን እንደሚከተለው ይናገራል ።

ጸላኤ ሠናያት ሰይጣን በአብርሃም በጎ ምግባር ስለ ቀና ሥራውን ለማደናቀፍ ራሱን የተፈነከተ በማስመሰል በጨርቅ አስሮ ሄዶ ከመንገድ ላይ ተቀምጠና እንግዳ ሰው ወደ አብርሃም ቤት ሲሄድ ወዴት ትሄዳለህ ብሎ ጠይቆ ወደ አብርሃም ቤት ነው የምሄደው ያለው እንደሆነ የቀድሞው አብርሃም መስሎሃልን እኔም ርቦኝ ጠምቶኝ ያበላኛል ያጠጣኛል ብዬ ብሄድ ራሴን ፈንክቶ ሰደደኝ በማለት እንግዶችን ይከለክልበት ጀመር ።

አብርሃም እንግዳን በማጣቱ ሁለት ቀን እህል ሳይቀምስ ጾሙን አደረ ፤ በሦስተኛው ቀን ሥላሴ በሦስት ሽማግሌዎች አምሳል መጥተው በድንኳኑ ደጃፍ ተቀመጡ አብርሃምም ባያቸው ጊዜ እጅግ በጣም ተደሰተና "ገሃሡ አጋዕዝትየ ቤተ ገብርክሙ አብርሃም" ጌቶቼ ወደ አገልጋያችሁ አብርሃም ቤት ገብታችሁ አረፍ በሉ አላቸው እነርሱም የአብርሃምን እንግዳ ተቀባይነት ስለሚያውቁ ስለደከመን አዝለህ አስገባን አሉት እሺ ብሎ አንደኛውን አዝሎ ወደ ድንኳኑ ቢያስገባው ሁለቱም በግብር አምላካዊ ከድንኳኑ ውስጥ ገብተው ስለአገኛቸው አምላክነታቸውን ለመረዳት ችሏል ።

አብርሃም ወዲያው ሣራን እንጀራ እንድታዘጋጅ አዝዞ እርሱም ከላሞቹ መካከል የሰባውን መርጦ አምጥቶ አርዶና አወራርዶ አቀረበላቸውና ከበሉ በኋላ ሣራ ሚስትህ ወዴት ናት ብለው ጠይቀው በድንኳኑ ውስጥ መኖሯን ስለነገራቸው "እመ ከመ ዮም እገብእ ኀቤከ ወትረክብ ለከ ሣራ ወልደ" እንደ ዛሬ የዛሬ ዓመት ወደ አንተ እመለሳለሁ ሣራም ልጅ ትወልዳለች አለው ሣራም ይህንን ቃል በሰማች ጊዜ ከት ብላ ሳቀች ምክንያቱም እርሷ የ፺ ዓመት ባልቴት ባሏ አብርሃም የ፻ ዓመት ሽማግሌ ስለነበር ሁላችንም አርጅተናል እንግዲህ ወዲህ ልጅ ለመውለድ እንዴት እንችላለን በማለት ነው ።

እግዚአብሔር አብርሃምን ሣራ ለምን ሳቀች በውኑ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለን ባለው ጊዜ ሣራ ፈራችና አልሳቅኩም ብላ የተናገረችውን ቃል በኋዛ ራሷ አስተባበለች ።

ሥላሴ በአብርሃም ዘንድ የእንግድነት ጊዜያቸውን ፈጽመው ወደ ሶዶም ጉዟቸውን ሲቀጥሉ አብርሃም ሊሸኛቸው ከእነርሱ ጋር ሔደ ሥላሴም የሶዶም ሰዎች ክፉ ሥራ በመሥራታቸው እንደሚያጠፋቸው ለአብርሃም ገልጸው ነግረውታል ዘፍ. ፲፰. ፩ ።

እንዲሁም መላእክት በሰዎች ተመስለው በእንግድነት ወደ ሎጥ ቤት ሄደው ነበር ከሎጥ ቤትም ደርሰው ከደጁ ተቀመጡ ሎጥ እንግዶቹን ባየ ጊዜ በጣም ደስ አለው ወደ ቤቱም ገብተው እግራቸውን ታጥበው እህል ውሀ ቀምሰው አረፍ ብለው አድረው ሲነጋ መንገዳቸውን እንዲቀጥሉ ለመናቸው ።

እነርሱም እሺ ብለው ወደ ሎጥ ቤት ገቡ እርሱም ለእንግዳ የሚያስፈልገውን መስተንግዶ ሁሉ አዘጋጅቶ አቀረበላቸው ነገር ግን በምድረ ሰዶም የሚኖሩ ሰዎች እንግዳን መቀበል የማይወዱ ተንኮለኞች ስለነበሩ የእንግዶቹን መምጣትና ከሎጥ ቤት ውስጥ መግባታቸውን ሰምተው ስለነበር በመንፈቀ ሌሊት ወደ ሎጥ ቤት መጥተው ቤቱን ዙሪያውን ከበቡና በእንግድነት የመጡትን ሰዎች አውጥቶ እንዲሰጣቸው ጠየቁት ፤ ሎጥ ግን እንግዶቹን አሳልፎ ላለመስጠት ከሶዶም ሰዎች ጋር በብርቱ ይታገል ጀመር የቤቱን ደጃፍ አጥብቆ ዘግቶ ለብዙ ሰዓት ሲታገል ከቆየ በኋላ በሰዎች አምሳል ተመስለው በእንግድነት መጥተው የነበሩት መላእክት በቤቱ ዙሪያ ተሰብስበው የነበሩትን የሰዶምን ሰዎች በጠቅላላ ከልሒቅ እስከ ደቂቅ ዓይናቸውን አሳወሯቸው ከዚያ በኋላ እንግዶቹ የነበሩበትን የሎጥን ቤት በዳበሳ ሊያገኙት ባለመቻላቸው የዓይናቸውንም ብርሃን አጥተው በእንግዶቹም ላይ አንዳች ጉዳት ሳያደርሱ በሐፍረትና በኀስቱልና ወደየቤታቸው ተመልሰዋል እንግዶቹን ተቀብሎ በክብር አስተናግዶ ያሳደረው ሎጥ ግን በዚያ ሀገር ላይ ከታዘዘው መዓት ከእነ ቤተ ሰቡ ለመዳን ችሏል አሪት ዘፍ. ፲፱ እግዚአብሔር አምላክ በነቢዩ ሙሴ ላይ አድሮ ስደተኛውን (እንግዳውን) አትጥላው የስደተኛው ነፍስ እንዴት እንደሆነች አውቃችኋል እናንተም ደግሞ በምስር ምድር ስደተኞች ነበራችሁና ብሏል ዘፀ. ፳፫.፱ እንዲሁም ።

ሐዋርያው ጳውሎስም ለዕብራውያን በጻፈው መልእክቱ "እንግዶችን መቀበል አትርሱ በዚህ አንዳንዶቹ ሳያውቁ መላእክትን በእንግድነት ተቀብለዋልና" ሲል ተናግሯል ዕብ. ፲፫.፪ ።

እንግዳ ተቀብሎ ማስተናገድ እንደ አብርሃምና እንደ ሎጥ ድኅነተ ሥጋን የሚያስገኝ ሲሆን ድኅነተ ነፍስንም እንደሚያሰጥ በቅዱስ መጽሐፍ ተጽፏል ።

እንግዳን ለመቀበልም በጎ ፈቃድን እንጂ ሀብታም ባለጸጋ አያሰኝም ባለጸጋ እንግዳን ተቀብሎ አብልቶ አጠጥቶ አልጋውን ዘርግቶ ምንጣፉን አንጥፎ ልብሱን አልብሶ አሳድሮ ሲነጋ ስንቅ ሰጥቶ መንገድ አሳይቶ ሸኝቶ ይሰዳል ፤ ድሃ የሆነ እንደሆነ ደግሞ ምንም የሚያበላው ባይኖረውም እንግዳውን ተቀብሎ ውሀ ቀድቶ እግሩን አጥቦ እሳቱን አንድዶ ጐዝጉዞ አስተኝቶ ካሳደረው በኋላ መንገድ አሳይቶ ይሰደዋል በሀብታሙም ሆነ በድኃው በኩል የሚፈጸመው የእንግዳ አቀባበል ተግባር ሁሉም ከፍተኛ ዋጋ ያለው ሲሆን ለዚህ መንፈሳዊ ተግባር ሁሉም መተባበር ይኖርበታል ።

ሀገራችን ኢትዮጵያ እንግዳን በመቀበል ረገድ በዓለም የታወቀች ዝነኛ ሀገር ናት በገጠሪቱ ኢትዮጵያ እንግዶች ለማደር ወደ ቤታቸው ሲሄዱላቸው የእንግዶችን እግር ለማጠብና ወደ ቤታቸው አስገብተው ለማሳደር የሚሽቀዳደሙ ሰዎች ይገኛሉ ይህም ሊናቅና ሊዘነጋ የማይገባው ዓቢይ ቁምነገር ነው ።

በአሁኑ ጊዜ በሀገራችን ላይ በደረሰው ከፍተኛ ችግር ምክንያት ከሚኖሩበት ቤት ወጥተው ወደማያውቁት ሀገር በመሄድ ለሰው እንግዶች ለሀገሩ ባዳዎች የሆኑ ወገኖቻችን እያሌ ናቸው ።

እነዚህ ወገኖቻችን ትልቁም ትንሹም በፍቅር ሊያስተናግዳቸው ይገባል ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ እናንተን የተቀበለ እኔን ተቀበለ እናንተን እንቢ ያለ እኔንም እንቢ አለ ብሎ እንዳስተማራቸው በችግር ምክንያት እንግዶች በመሆን የሚንከራተቱትን ተቀብሎ በምግብም በልብስም የሚያስተናግድ ክርስቶስን ተቀብሎ እንዳስተናገደ ይቆጠራል ።

ማንኛውም ሰው በዚህ ዓለም ላይ ለመኖር የሚችለው ለዘለዓለም ሳይሆን ለተወሰነ ዘመን ነው በዚህ ዓለም የሚኖረውም ዘመን የእንግድነት ዘመን ተብሎ ይጠራል በታሪክ ተጽፎ እንደ ምንመለከተው ያዕቆብ በረኃብ ምክንያት ወደ ምድረ ግብፅ በተሰደደ ጊዜ ፈርዖን ዕድሜህ ምን ያህል ነው ? ብሎ ቢጠይቀው የእንግድነቴ ዘመን መቶ ሰላሳ ነው በማለት በዚህ ዓለም የሚኖረውን ኑሮ የእንግድነት ዘመን በማለት ገልጾታል ።

እንግዲህ ይህ ዓለም በእንግድነት እንጂ በቀዋሚነት ለመኖር የማንችልበት ዓለም መሆኑን ማወቅና መረዳት ይኖርብናል ስንኖርም እንግዳን በመቀበል በመረዳዳትና በመተዛዘን ሊሆን ይገባል ።

ከላይ እንደተመለከትነው አብርሃምና ሣራ እንግዶችን ሳይሰለቹ አዘውትረው በፍቅር ከመቀበላቸው የተነሣ ሥላሴን የማስተናገድ ዕድል ገጠማቸው መካነው የነበሩትም ልጅ አገኙ ያገኙትም ልጅ ለፈጣሪው የሚገዛ ለወላጆቹ የሚታዘዝ ሆነ ሥላሴም ከአብርሃም የምሠውረው ምሥጢር የለም ብለው የሰዶምንና የገሞራን ጥፋት ገለጹለት ።

አሁንም ቢሆን እንግዶችን ተቀብለው በሚገባ የሚያስተናግዱ ሰዎች እንደ አብርሃም ቤታቸው ይባረካል እንደ ይስሐቅ ያለ ለፈጣሪው የሚገዛ ለወላጆቹ የሚታዘዝ የተባረከና የተቀደሰ ልጅ ሊያገኙ ይችላሉ እንዲሁም እንደ ሎጥ ከታዘዘ መቅሠፍትም ለመዳን የሚቻለው የሚበላው የሚለብሰው አጥቶ ከሀገር ወደ ሀገር ከመንደር ወደ መንደር የሚንከራተተውን እንግዳ ተቀብሎ በማስተናገድ ነው በሎጥ ቤት የነበሩትን እንግዶች ለመቃወም ተሰብስበው የነበሩት ሰዎች በጠቅላላ ዓይነ ዕውራን እንደሆኑ አሁንም እንግዶችን በመቃወም የሚነሣ ሁሉ ይህንን የመሰለ መከራ ይጠብቀዋል ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክር

ወደ ገጽ ፳ ዞሯል



# ደብዳቤዎች

ከገጽ ፩ የዞረ

ድንግል ማርያምን በግል በሚያከብሩበት ወቅት ስዕሉን አምጥተው በስዕሉ ፊት ሻማ ማብራታቸው ለአክብሮና ከልብ በመነጨ ፍቅር የሆነ እንጂ የዚህ ዓይነት ተግባር ወደ አምልኮ የሚመራ አይደለም ። እንዲያውስ በመስቀል ደመራ የምናከብረው በትንሣኤ ወንዱም ሴቱም ወጣቶቹም ሆኑ ሕፃናቱ በቤተ ክርስቲያን ጧፍ አብርተው ቤተ ክርስቲያኑን የሚዞሩት ለምን ይመስልሃል የደስታ መግለጫ አይደለምን ስለዚህ በስዕሎች ፊት ለፊት መብራት የሚበራው ለአክብሮትና የፍቅር መግለጫ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል ።

ይልቁንም ተገቢ ያልሆነ በከንቱ ስለሚበራው ሻማ በዚህ አጋጣሚ እንግለጽልህ ሴቶቹ ሻማ ይገዙና ቤተ ክርስቲያን መጥተው ከውስጥ ሳይሆን ከውጭ አቃጥለውት ይመለሳሉ ይህ ታላቅ ስሕተት ነው ። ሻማና ጧፍ የሌላቸው አብያተ ክርስቲያናት ሞልተዋል ታድያ ሻማው ሳይጸለይበት ሳይወደስበት በጠቅላላ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ሳይውል ከቅጽረ ቤተ ክርስቲያን አቃጥሎ መሄድ ለምን ይሆን? የዚህ ዓይነት ተግባር ከፍ ያለ ስሕተት ስለሆነ ቢተውት መልካም ነው ካመጡት ቤተ ክርስቲያን እንዲገለገልበት ለቤተ ክርስቲያን መስጠት እንጂ ማቃጠል አያስፈልግም የዚህ ዓይነት ተግባር በደል ይባላል እንጂ በስዕል ፊት መብራት ማብራት ኃጢአት እንዳይደለ እንገልጽልሃለን ።



www.ethiopianorthodox.org

# የቤተሰብ ዓምድ

## የቤተሰብ አመሠራረትና መዋቅር

“ቤተሰብ አንድ ትንሽ መንግሥት ነው” የሚል አነጋገር (ዘይቤ) ያለ ምክንያት የሚወረወር አይደለም ። ኅብረተሰብ ወይም ሕዝብ ራሱ የብዙ ቤተሰብ ድምር ነውና ። ስለዚህም ገና ከመሠረቱ ጀምሮ ጥንቃቄ የተሞላበትን ጥበባዊ የአመራር ስልትን ይጠይቃል።

እነሆ ዛሬ አንድ ሰው ለታላቅ ቁም ነገር ወይም ለሥራ ኃላፊነት ወይም ለከፍተኛ መንፈሳዊ አገልግሎት ሲታጭ ከሚያሟላቸው መመሪያዎች አንዱ ቤተሰቡን በመልካም ሁኔታ መምራትና ማስተዳደር ይችላል ወይ ? የሚል ጥያቄ አስከትሏል ። ሐዋርያ ጳውሎስም ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ደቀ መዝሙሩ ጢሞቴዎስ በጻፈበት መልእክት ምዕ. ፫. ለቅስና ማዕርግ መመረጥ ስለሚገባው ሰው ሲናገር ይህንኑ አጉልቶ ገልጾታል ።

ቤተሰብ የሚመሠረተው “ባልና ሚስት” ተብለው በሚጠሩ ሁለት ጾታዎች ሆኖ ልጆች በተወለዱ መጠን ዘርፍ እየሰፋ የሚሄድና አመራሩ ላይም ክብደት እየጨመረ መምጣቱ አያከራክርም ። የሚስት ወይም የባል እኅቶችና ወንድሞች ወይም የሥጋ ዝምድና ያላቸው ሌሎችም ወይም የሙት ልጆች ሲታከሉበት አሁንም ሌላ ክብደት ያመጣል ። ይህኑ ሁሉ አስተባብሮ ለመምራት ከመቻል የበለጠ የሥራ መፈተኛ የለም ።

ሌላው የቤተሰብ አመራር ችግር ከፍተኛ ደረጃ ላይ የሚደርሰው ደግሞ ከባልና ሚስት መካከል እንደፍችና ከዚህ ዓለም በሞት ወይም አንድ ወንድ ለአንዲት ሴት፣አንዲት ሴት ለአንድ ወንድ የሚለው የተፈጥሮ ሕግ ተሽሮ ባልና ሚስት እንደፈለጋቸው ንብረት በማባከን ባሻቸው አዳሪዎች ሆነው ትዳር ይፈርስና በዚያው በተከፋፈለ ንብረት ሌላ ዓይነት ቤተሰብ መመሥረት ሲሞከር የልጆችም ዕድል አብሮ ይበላሻል ። ጣውንትና ጣውንት ፣ የእንጀራ ልጅነት ፣ የእንጀራ አባትነትና እናትነት የተሠኙ ባዕዳን የቅራኔ ምልክቶች መታየት ይጀምራሉ ።

የእንጀራ እናትና የእንጀራ አባት የተሠኙት መጠሪያዎች ከተነሡ ዘንድ እኔ ራሴ እንኳ የደረሰብኝን በደል ባወሳ ታላቅ ስንክሣር ይወጣዋል ። ብዬ አምናለሁ ። ይኸውም በመሠረቱ አባቴ የሞተው በልጅነቴ (በሕፃንነቴ) ሲሆን እናቴ ብቻዋን እኔን በማሳደግ ያየችው አበሳ ይህና ይህ ነው።ተብሎ ለመተንተን ቃላት ያጥሩኛል።ምክንያቱም ዘመኑ ጠላት ከኢትዮጵያ ተጠራርጎ የወጣበት ወቅት ሲሆን በጦርነት የፈራረሰችውን አገር እንደገና ለማቋቋምና የሕዝቡን ሥርዓተ ኑሮ ለማደላደልና በጦርነቱ ጊዜ ከተከፈለው መሥዋዕትነት ይበልጥ ግራ የሚያጋባ ችግር እንደነበረበት ማንም ያውቀዋል ። ከዚህም የተነሣ ጠላት እንደ ወጣ ቀድሞ በፋሽሽቶች መደለያ ደመወዝ ይተዳደር የነበረው ሁሉ አበሉም ሆነ ጉርሻው ሲቋረጥበት ሌላ መተዳደሪያ እስከሚያገኝ ድረስ መቋቋሚያ አጥቶ ከአንዱ አውራጃ ወደ ሌላው መሰደድ ፣ አሽከርነትና ሎሌነት ወይም ግርድና ማደር ግድ ሆኖበት ነበር ።

ይህን ዓይነቱን የመከራ ገፈት ከቀመሱት ኢትዮጵያውያን መካከል አንዷ የእኔ እናት ነበረች ታዲያ የሥርዓተ ኑሮ ምስቅልቅል መውጣት ግራ ባጋባት ጊዜ ከተወለደችበት አውራጃ እኔን አዝላ በመራቤቴ አውራጃ ልዩ ስሙ ሚዳ ተብሎ ወደሚጠራው ወረዳ ገባች በዚያም እርስዋ ሌላ ባል አግብታ ስትኖር እኔን ወደ ተወለድሁበት ቀበሌ በመመለስ ለአባቴ ትንሽ ወንድም አደራ ሰጠችኝ።ታዲያ ሁለታችንም ፩ እኔ በምራት እጅ ስምንት ዓመት ሙሉ ቁርስ ምሳና እራት ፣ ወይም መቆያ (መክሰስ) የሚባሉትን ቃላት ተግባራዊ ትርጉማቸውን ሳላውቅ የዛፍ ፍሬ እየተመገብሁ ፣ እንደከብት ራቁቴን ከከብት ጋር እየተሰማራሁ ማር አልበላሁም እንጂ ከእንስሳት ባልተለየ ሕይወት ማደግ አይቀርምና አደግሁ ልበል መሰለኝ ።

፪/ እናቴ ደግሞ በበኩሏ የመሠረተችው ትዳር ምንም ደስ የማይል ከመሆኑ የተነሣ አቶ ባል ሌላ ሚስት በላይዋ ላይ ለመያዝ ፈልጎ ስለነበር በመካከል ቤት የኔይቱም “እናት ኃይለኛ ነበረችና ሁለቱ እስስት ለእስስት ተናንቀው ሊተላለቁ ለሠፈር ለሀገር ያስቸገረ ፈተና ገጥሟት እንደነበር ትዝታው አይረሳም ። ስለዚህም በየሠርጉ ቤት ዘፈን ሲጀመር የእኔ እናትና ጣውንቷ የሚሰዳደቡበት መድረክ ተከፍቶ ሁኔታው ሲያስቅም ሲያሳዝንም መኖሩ ይታወሳል ። ለምሳሌም አንዱን ልጥቀስላችሁ ፣ ይሕውም የእኔይቱ እናትና ጣውንትዋ በአንድ ሠርግ ቤት ይገናኛሉ ። ዘፈን ሲጀመር ጣውንትዋ ቀድማ አታሞ ትይዝና የእኔን እናት እንደ አንድ የሀገር ስደተኛ አድርጋ በመቁጠር ።

“ስደተኛ ሚስትህ የሞተች እንደሆን ቤተ ክሲያኑ የእኛ የት ትቀብራት ይሆን” ስትል የእኔ እናት ቀበል አድርጋ አንቺን ማን አረገሽ የሰውን ስም አጥፊ በየደረስሽበት ገበታ አራጋፊ” በማለት በቅልውጥ አዳሪ መሆንዋን ስትገልጥባት በዚሁ ሳቢያ የተነሣው ፀብ ለብዙ ሰው ሕይወት በከንቱ መጥፋት ምክንያት ሆኖም እንደ ነበር አስታውሳለሁ ።

እንግዲህ ይህን ለመግለጥ የፈለግሁበት ምክንያት በአጋጣሚ ችግር ምክንያትም ይሁን ወይም በቅንጦት የአንድ ዓይነት ትዳር መሠረት ሲናጋ ጣሪያና ግድግዳውም አብሮ ሲደረመስ የዚያ ቤተሰብ አባል የሆነ ሁሉ ምን ያህል አበሳ እንደሚገጥመው ለመጠቆም ያህል ነው ።



በተለይም የእንጀራ አባትና የእንጀራ እናት ጉዳይ ለልጆች የቱን ያህል መቅሠፍት እንደሆኑ የሚያውቅ ያውቃቸዋል ። ፍሬ ነገሩን ከሚከተሉት የቅኔ ግጥሞች መመልከት ይቻላል ።

“እናት የሌለው ልጅ መራር እንደጌሾ
ሳይሰርቅም ሌባ ነው ባይናገር ዋሾ
ረኀቡ በሆዱ አድጎ ዘረዘረ
እናቴ ብትኖር ታጭድልኝ ነበረ።
አያድርስባችሁ ደርሶብኛል በእኔ
የእንጀራ እናት ከፉ የአባት አረመኔ’
ሲል የሚኖረው ያለ ምክንያት አይደለም ።

ስለዚህ የቤተሰብ መሠረታዊ አቅዋምና መዋቅር አለመስተካከል ጉዳቱ በዚያ ቤተሰብ ውስጥ ባሉት አባላት ዘንቦ አያባራም ወደ ኅብረተሰቡም የመዛመት ጠባይ አለው ።

እንዲህ ከሆነ የተበታተኑ ቤተሰቦች በሕይወት መኖራቸው ከተረጋገጠ የተለያዩትን ለማገናኘትም ጭምር የተለየ ጥረት እንዲታከልበት የአብያተ ክርስቲያናት እርዳታ አድራሾች ሁሉ ሊያጤኑት ይገባል።ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖርም ተብሎ የተጻፈው የወንጌል ቃል እዚህም ላይ ሊጠቀስ ይገባል።ከእናት ከአባታቸው የተለዩ ልጆች ከልጆቻቸው የተለዩም ወላጆች በምግብና በመጠለያ ማግኘት ብቻ ላይረኩ ይችላሉ ። ስለዚህ ቤተክርስቲያን ከምታሳድጋቸው ፳ሺ፤ ሕፃናት መካከል አብዛኞቹ የሚቻል ከሆነ ከወላጆቻቸው የሚገናኙበትን ዘዴ ጭምር እንደምታጠና ተስፋ ይደረጋል ። ሁሉን ቻይ የሆነ አምላክ ይህን ሁሉ የፈተና ወቅት አሳልፎልን የተበታተኑ ልጆችና ወላጆች የተለያዩም ባልና ሚስት ተገናኝተው የፈረሱ ትዳሮች እንደገና ተመሥርተውና ተዋቅረው ለማየት ያብቃን ። አሜን ።

መ/አእ. መክብብ አጥናው

# በሬና ገበሬ ዘርና መሬት

በንቃቱና በትጋቱ የታወቀ ገበሬ ቢኖር ጠምዶ የሚያርሳቸውን በሮች ካላገኘ የእርሱ ትጋትና ንቃት ውጤት አይኖረውም ።

እንደዚሁም ሲያርሱ ውለው ሲያርሱ ቢያድሩ ድካም የማይሰማቸው በሮችም ቢኖሩ የሚያርስባቸው ገበሬ ካላገኙ የበሮቹ መኖር ብቻ ምርት ሊያስገኝ አይችልም ።

እጥጋቢ ምርትና ተፈላጊ በረከት ሊገኝ የሚቻለው በሬና ገበሬ ሲገናኙ ነው ፣ በሬና ገበሬ ቢገናኙና በሥራ ቢስተካከሉም ቅሉ ዘርና መሬት ደግሞ ሲዛመዱ ነው እስንዴ የሚሆነውን በቃ በቆሎ ቢዘራ ወይም ለበቆሎ የሚሆነው ስንዴ ቢዘራበት ከድካም በስተቀር የሚፈለገውን ምርት ለማግኘት አይቻልም ።

ሥራው የተሟላ እንዲሆን ምርቱም እንዲበረከት ከተፈለገ ግን አስቀድሞ መሬቱ ምን ዓይነት እህል ቢዘራ መልካም ውጤት እንደሚያስገኝ መመርመርና እንዴት ያለ እህል እንደሚዘራ ማጥናት ያስፈልጋል ። ስንዴ የሚያበቅል እንደሆነ ወይም የማያበቅል መሆኑን ከተጠና በኋላ አስፈላጊውን ዘር ሲዘሩት ድካሙ ከንቱ ሁኖ አይቀርም የድካም ዋጋ ይገኝበታል ማለት ነው ።

ዋናው ፍሬ ነገር መልካም ምርት መልካምም ፍሬ ሊገኝ የሚቻለው ሥራና ሠራተኛ በወቅቱ አንድ ላይ ሲገናኙ ነው።እንግዲህ ትጉህ ገበሬ በበጋ ወራት የፀሐዩን ሙቀት የሌሊቱን ብርድ ሳይሰቀቅ እሾሁን መንጥሮ ድንጋዩን ለቅሞ መሬቱን በሚገባ ከደለደለና በመልካም ሁኔታ ካለሰለሰ በኋላ ለደከመበት ቦታ የሚስማማውን ምርጥ የሆነውን ዘር ቋጥሮ የዝናምን መምጣት ተጠባብቆ ዝናም ሲጀምር የቋጠረውን ዘር የመዝራት የገበሬ ፋንታ ነው ። ገበሬ በሥራው ከተጋና ከነቃ የሰውን እጅ አይመለከትም የሰውን እጅ የሚመለከትና ለመቀበል እጁን የሚዘረጋ ሰነፍ ብቻ ነው ።

ጠቢቡ ሰሎሞንም ትጉህ ገበሬንና ሰነፉን ገበሬ እያነጻጸረ ሲናገር “የታካች እጅ ችግረኛ ታደርጋለች የትጉህ እጅ ግን ባለጠጋ ታደርጋለች ብሏል ምሳ. ፲ ፣ ፬ ። በሰሎሞን አባባል አሁንም የሰው ሽክም የሀገርም ችግር ሁነው የሚገኙት ትጉሆች ሠራተኞችና ገበሬዎች ሳይሆኑ ሥራ ፈቶች ናቸው ።

ሐዋርያው ጳውሎስም መሬት ዝናም ካልጠገበች አንድም ነገር እንደማታስገኝ አስመልክቶ ሲጽፍ “ብዙ ጊዜ በእርስዋ ላይ የሚወርደውን ዝናም የምትጠጣ መሬት ለሚያርስዋት የምትጠቅም አትክልትን የምታበቅል ከእግዙአብሔር በረከትን ታገኛለችና ካለ በኋላ የተዘራውን እህል ትታ እሾህንና ኩርንችትን ብታበቅል ግን የተጣለች ትሆናለች ብሏል ። ዕብ ፮ ፣ ፯ ።

በእውነቱ ከመሬት ጋር በእርሻ የሚታገል ሰው የድካሙን ዋጋ ከማግኘቱም በላይ በሰውም ቢሆን ከፍተኛ ምስጋና አለው እንዲያውም የሰው ልጅ ከመሬት ጋር ቢታገል ምን ያህል ክብር እንደሚያገኝ ዳግማዊ ምኒልክ የተናገሩትን ብናስታውስ መልካም ይመስለኛል።ሰው ሁሉ ለሌሎች ከሚገዛ ለእኛ ቢገዛ ክብር ያገኛል ነገር ግን ለእኔ ከሚገዛ ደግሞ ለመሬት ሎሌ ቢሆን የበለጠና እኔ ከምሰጠው ክብር በላይ ሊከበር ይችላል ብለዋል እውነትም በእርሻ ለመሬት የተገዛ የዕለት ጉርሱንና የዓመት ልብሱን ስለማያጣ ባጭር ተጥቆ ይረስ እንላለን ።

ክነፈ ርግብ ግርቆስ



www.ethiopianorthodox.org

# ዜና ሊቃውንት

በዛሬው ዜና ሊቃውንት ዓምዳችን
የምናቀርብላችሁ ስለ አለቃ መዝሙር
ዘዳዊት አጭር የሕይወት ታሪክ ይሆ
ናል ።

አለቃ መዝሙር ዘዳዊት ከአባታቸ
ው ከአለቃ ገብረ መድኅንና ከእናታቸ
ው ከወይዘሮ አስካለ ወልደ ጊዮርጊስ በ
ሸዋ ክፍለ ሀገር በሰላሌ አውራጃ አሊ
ዶሮ አቦ ከሚባለው ሥፍራ በ፲፰፻ ፺፪
ዓ.ም ተወልደው በዚያው በእናትናአባ
ታቸው ቤት ከአደጉ በኋላ ዕድሜአቸው
ለትምህርት ሲደርስ ሊመን ሥላሴ ከነ
በሩት መምህር ወልደ ሚካኤልና እን
ዲሁም በተለያዩ ሥፍራዎች ከሚገኙ
መምህራን ዘንድ በመሄድ ድጓ ፣ ጾመ
ድጓ ፣ ቅኔ ፣ አቋቋምና ዝማሬ ፣ መዋሥ
ዕት በተጨማሪም የብሉይና የሐዲስን
ትርጓሜ በሚገባ ጠንቅቀው ተምረዋል

ወላጅ አባታቸው አለቃ ዳዊት ገ/መ
ድኅን ጥንታዊ ሠዓሊ ስለነበሩና በጊዜ
ውም የሊመን ሥላሴን ቤተ ክርስቲያን
ሥዕል ይሠሩ ስለነበር አለቃ መዝሙር
ይህንን ዘመን የማይሽረውን ጥበብ ከአ
ባታቸው ጋር በትኩረት ሲቀስሙ ቆይ
ተው ዕውቀታቸውን በይበልጥ ለማዳ
በር ሲሉ በታላቁ ገዳም በደብረ ሊባኖስ
ይኖሩ ከነበሩትና በሠዓሊነታቸው በጣ
ም ታዋቂ ከነበሩት ከመልዓከ ሰላም ሉ
ቃስ ዘንድ ሄደው የሥዕል ሙያቸውን
ለማሻሻል እንደመጡ ቢገልጹላቸው
መልዓከ ሰላም ሉቃስም በደስታ ተቀብ
ለው በማስተማር ላይ እንዳሉ የአለቃ
መዝሙርን የሥዕል ጥበብ በተመለከቱ
ጊዜ በጣም አድንቀው አንተ ከኔ ብትበ
ልጥ እንጂ ከእኔ የምትሻውም ምንም አ
ይኖርም በማለት የምስክር ወረቀት ሰጥ
ተው በክብር ሸኝተዋቸዋል ። በዚህም
ጊዜ (ልውል) ራስ ካሣ ዳርጌ የጫጋል
መድኃኔ ዓለምን ቤተ ክርስቲያን ሥዕ
ል እንዲሥሉ ስለጠየቋቸው ሥራውን
በሚገባ ሠርተው በማስረከባቸው (ል
ውል) ራስ ካሣ በጣም ተደስተው ታላቅ
ሽልማትና ስጦታ አድርገውላቸዋል ።

በተጨማሪም ከእርሳቸው ጋር ተቀም
ጠው ከልጆቻቸው ጋር የፈረንሣይ ት
ምህርት እንዲማሩ ስለፈቀዱላቸው ት
ምህርቱን በሚገባ ሲከታተሉ ሣለ በሥ
ዕል ሥራ ምስጉንነታቸው በቤተ ክህነ
ቱም ሆነ በቤተ መንግሥቱ በጣም ታወ
ቀው ስለነበር ንግሥተ ነገሥታት ዘው
ዲቱ ከራስ ካሣ ዘንድ አስወስደው የመ
ናገሻ ማርያምን ቤተ ክርስቲያን የው
ስጥ ሥዕል እንዲሥሉ አዘዋቸው ስለ
ዋል ሥራውን በመልካም ሁኔታ ሠር
ተው ሲጨርሱ ሽልማትና ስጦታ አድ
ርገውላቸው ምድብ ሥራቸው በቤተ
መንግሥት እንዲሆን ተደረገ ። ከዚያም
በኋላ ሀገራችንን ኢትዮጵያን ጠላት በ
ወረራት ጊዜ ከጓደኞቻቸው ከአቶ እምአ
ዕላፍ ኀሩይ ጋር ሆነው ማይጨው ዘም
ተው ተመልሰዋል ።


አለቃ መዝሙር ዘዳዊት

ከዚያም ወዲህ በጅባትና ሜጫ አው
ራጃ ኤጀርሣ ለፎ ከሚባለው ቦታ በአ
ርበኝነት ሲዋጉ ቆይተው በኋላም ወደ
ደብረ ብርሃን ከተማ ተዛውረው የደ
ብረ ብርሃን ሥላሴን ቤተ ክርስቲያን
የውስጥ ሥዕል እየሠሩ ከሚያገኙት ገን
ዘብ በደብረ ብርሃንና በመንዝ አካባቢ
ለዘመቱት አርበኞች ስንቅና ጥይት እየ
ገዙ በማቀበል አምስቱን የጠላት ወረራ
ዘመን በውስጥ አርበኝነት አሣልፈዋል



ኢትዮጵያ ሀገራችን ነፃነቷን ስትጐ
ናጸፍ በወቅቱ ፓርላማ ይባል የነበረው
ንና የቅድስት ሥላሴን ሥዕል እንዲሠ
ሩ ስለታዘዙ ከአቶ እምአዕላፍ ኅሩይና
ከሌሎች ጓደኞቻቸው ጋር በመሆን በ
ሚገባ ሠርተው አሥረክበዋል ። ከዚ
ያም በኋላ ቋሚ ሥራቸው በቤተ መንግ
ሥቱ ቅጥር ግቢ በሚገኘው ቁም ጽ/ቤት
ውስጥ ስለተደረገ ዕድሜያቸው ለጡረ
ታ ብቁ እስካደረጋቸው ድረስ በሙያቸ
ው የክፍሉ ሥራ አስኪያጅ ሆነው ሲሠ
ሩ ቆይተዋል ።

አለቃ መዝሙር ዘዳዊት ከሠሯቸው
ሥራዎች አንዳንዶችን ለመጥቀስ ያህ
ል ፡-

፩ኛ/ የሊመን ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን
ግንቡ ፈራርሶ በቅድስቱ ብቻ ይኖር ስለ
ነበር የፈረሰውን በግል ገንዘባቸው ግን
ቡን እንደገና አሠርተዋል ። ስለዚህም
የአካባቢው ነዋሪ ሕዝብ የሃይማኖት
አባታችንና አሣቢያችን በማለት ይመ
ካባቸው ነበር ።

፪ኛ/ በሰላሌ አውራጃ የምትገኘው
የአራተ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፈርሶ
ታቦቷ ለብዙ ዘመን በመቃኞ በመኖሯ
ከግል ገንዘባቸው በጥሬ ገንዘብ ብር፲፰
ሺ (አሥራ ስምንት ሺ) በመስጠትና በ
ተጨማሪም ለቤተ ክርስቲያኑዋ የሚ
በቃ ቆርቆሮ እና ልዩ ልዩ መሣሪያዎች
ን በማቅረብና የአካባቢውን ምዕመና
ንና ከአዲስ አበባም አንዳንድ በጐ አድ
ራጊዎች ምዕመናንን በመቀስቀስ
የቤተ ክርስቲያኑዋ ሥራ በሚገባ ከተ
ጠናቀቀ በኋላ አሁንም ከግል ገንዘባቸ
ው ፲፰ ሺ ብር የፈጀ ሥጋጃ ምንጣፍና
አበባ ምንጣፍ ገዝተው በማበርከት ታ
ቦቷ ወደ አዲሱ ቤተ ክርስቲያን ብፁዕ
ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖትና ሌሎ
ችም ሊቃነ ጳጳሳት በተገኙበት ገብታ
ለች ። አለቃ መዝሙር ለዚህች ቤተክር
ስቲያን ሥራ ከ፴፰ ሺ ብር በላይ አስተ
ዋፅኦ አድርገዋል ።

፫ኛ/ በአሥመራ ከተማ የአሥመራ ማር
ያምን የውስጥ ሥዕል ከፊሉን በራሳቸ
ው ወጪ

፬ኛ/ የጫጋል መድኃኔ ዓለምን የውስጥ
ሥዕል በመንግሥት ትዕዛዝ

፭/ኛ የመናገሻ ማርያምን የውስጥ ሥዕ
ል በመንግሥት ትዕዛዝ

፮/ኛ ሐረር አደሬ ጢቆ ሥላሴን የውስጥ
ሥዕል በመንግሥት ትዕዛዝ

፯ኛ/ በአሰላ ከተማ የቅዱስ ሚካኤልን
የውስጥ ሥዕል በመንግሥት ትዕዛዝ

፰ኛ/ የቅዱስ ላሊበላን የውስጥ ሥዕል
ከፊሉን በራሳቸው ገንዘብ

፱ኛ/ የግሽን ማርያምን የውስጥ ሥዕል
ከፊሉን በራሳቸው ገንዘብ

፲ኛ/ የቀጨኔ መድኃኔ ዓለምን የውስጥ
ሥዕል ከፊሉን በራሳቸው ገንዘብ

፲፩ኛ/ የቅድስት ማርያምን የውስጥ ሥ
ዕል በሙሉ በራሳቸው ገንዘብ

፲፪ኛ/ የየካ ሚካኤልን ቤተ ክርስቲያን
የውስጥ ሥዕል ከፊሉን በራሳቸው ገን
ዘብ

፲፫ኛ/ የግቢ ኪዳነ ምህረትን የውስጥ
ሥዕል ከፊሉን በራሳቸው ገንዘብ

፲፬ኛ/ የጉፋ ቅዱስ ገብርኤልን ቤተ ክ
ርስቲያን የውስጥ ሥዕል

፲፭ኛ/ በወለቃ የቅዱስ ገብርኤልን ቤተ
ክርስቲያን የውስጥ ሥዕል

፲፮ኛ/ የብሥራተ ገብርኤልን ቤተ ክርስ
ቲያን የውስጥ ሥዕል

፲፯ኛ/ የሰበታ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅ
ዱስን ቤተ ክርስቲያን የውስጥ ሥዕል

፲፰ኛ/ የቀበና አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱ
ስን ቤተ ክርስቲያን የውስጥ ሥዕል

፲፱ኛ/ አዲስ አበባ የልደታ ማርያምን
ቤተ ክርስቲያን የውስጥ ሥዕል

፳ኛ/ አዲስ አበባ የእግዚአብሔር አብን
ቤተ ክርስቲያን የውስጥ ሥዕል

፳፩ኛ/ የጐላ ቅዱስ ሚካኤልን ቤተ ክር
ስቲያን የውስጥ ሥዕል

፳፪ኛ/ በበዓታ ቤተ ክርስቲያን

ሀ/ የታላቁ ጀግና የአፄ ምኒልክን ፎ
ቶግራፍ በሥዕል

ለ/ የእቴጌ ጣይቱን ፎቶግራፍ በሥ
ዕል

ሐ/ የንግሥት ዘውዲቱ ምኒልክን
ፎቶግራፍ በሥዕል

መ/ የልጅ እያሱ ምኒልክን ፎቶግራ
ፍ በሥዕል

በተጨማሪም በኢትዮጵያ ታላላቅ ገዳ
ማትና አድባራት እንዲሁም በአዲስ አ
በባ ከተማ ውስጥ በሚገኙ አብያተ ክር
ስቲያናት በየመንበሩ ላይ የሚገኘውን
የእመቤታችንን ሥዕል በግል ገንዘባቸ
ው በመሥራት አድለዋል ።

፳፫ኛ/ በሞስኮ ቤተ ክርስቲያን በአድና
ቆትና በክብር የተቀመጠችውን ሥዕለ
ማርያም ሠርተዋል

፳፬ኛ/ በኢየሩሳሌም ፡-


አለቃ መዝሙር ከሣሏቸው ሥዕሎች አንዱ

ሀ/ በጎልጎታ መድኃኔዓለም ቤተ ክ
ርስቲያን የንግሥተ ሰባን ታሪካዊ ሥዕ
ል

ለ/ በዓልዓዛር ተክለሃይማኖት ቤ/ክ
የውስጥ ሥዕል በሙሉ

ሐ/ የኢያሪኮ ሥላሴን ገዳም የውስጥ
ሥዕል በሙሉ በነፃ ሠርተው አስረክበ
ዋል ።

አለቃ መዝሙር ዘዳዊት በ፲፱፻፶፯
ዓ.ም እና በ፲፱፻፶፱ ዓ.ም. ከባለቤታቸ
ው ጋር ኢየሩሳሌምን የጐበኙ ቢሆ
ንም ፣ በዚች ቅድስት ሀገር የሥዕል ሥ
ራቸውን ባለማኖራቸው ለኢየሩሳሌም
ገዳማትና ማኅበራት ዕድገት እጅግ ይጥ
ሩ የነበሩት በጊዜው የነበሩት የኢየሩሳ
ሌም ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ማቴዎስ ደ
ጋግመው ስለጠየቋቸው በ፲፱፻፷፯ ዓ.ም
ወደ ኢየሩሳሌም ሄደው ከፍ ብሎ የተጠ
ቀሱትን የሥዕል ሥራዎች ሠርተዋል።

በዚህም ጊዜ ቀደም አድርገው የሠሯ
ቸውን የንግሥት ሳባን ታሪካዊ ሥዕሎ
ችን የዓለም ቱሪስት እንደጐርፍ ውሃ
ያለማቋረጥ በሚጎበኘው በጐልጐታ
መድኃኔ ዓለም አኑረው ስለነበረ የዓለ
ም ጐብኚዎች ይኸን ሥዕል የሠራው
አፍሪካዊ ሠዓሊ የት ነው የሚገኘው ?
እያሉ በመጠየቅ አለቃ መዝሙር ከሚ
ሠሩበት ሥፍራ ድረስ በመሄድ በአድና
ቆት ይመለከቱ ነበር ። ይህም ሥራቸው
ኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን መላውን አፍ
ሪካን ጭምር የሚያኮራ በመሆኑ በዓለም
ቱሪስቶችና በሌላው ጐብኚ ዘንድ ኢት
ዮጵያ ሀገራችንንና ሠዓሊ መዝሙር ዘ
ዳዊትን ዛሬም ሆነ ወደፊት ሲያስታው
ስ ይኖራል ።

አለቃ መዝሙር ዘዳዊት አሁንም አ
ልሞቱም ማለት ያስችለናል ፣ ምክንያ
ቱም ይህንን ለዛ ያለውንና ያየውን ሁሉ
የሚማርክ የሥዕል ሙያቸውን ይዘውት
ከምድር በታች አልዋሉም ፣ ልጃቸው
ተስፋዬ መዝሙርን በጥበባቸው አስታ
ጥቀውት አልፈዋል ፣ በመሆኑም ልጃ
ቸው አቶ ተስፋዬ መዝሙር ካላቸው
መደበኛ የመሐንዲስነት ሙያ ጋር የሥ
ዕልን ሥራ ጠንቅቀው ያወቁ በመሆናቸ
ው አሁን ለመጨረሻ ጊዜ አባታቸው
አለቃ መዝሙር ዘዳዊት ሊሠሩ ያቀዱ
ትን ሆነ ጀምረው ያልፈጸሙትን ሥራ
ሁሉ ብዙ ዘመን የጣሏትን የሥዕል ቡር
ሽ አንስተው ባላቸው ትርፍ ጊዜ ውስጥ
ሠርተው አሥረክበዋል ።

የአባታችን የአለቃ መዝሙርን ትገ
ታ አሁንም ከፊታችን እንዳይጠፋ በማ
ድረጋቸው ለካ አልሞቱም እያልን እን
ጽናናለን ።

አለቃ መዝሙር ዘዳዊት በሕይወታ
ቸው ዘመን ሙሉ እንግዳ ተቀባይ ፣ ያጡ
ና የተቸገሩትን ባላቸው አቅም ሁሉ መ
ርዳት የሚወዱ ፣ ምንጊዜም ቢሆን ለቅ
ን ተግባር ዛሬስ በቃኝ ስለቸኝ የማይሉ፣



www.ethiopianorthodox.org

በተፈጥሮአቸው እርጎሩጎና ቸር፣ ስለነ
በሩ የዕለት ምግባቸውን እንኳን የእግዚ
አብሔር ታዛቢ እንግዳ በማዕዱ ላይ ካ
ልኖረ (ካልተገኘ) አልበላም እንሱት
ብለው እንግዳ የሚጠባበቁ ፥ መጪ እን
ግዳ ከጠፋ ከቤታቸው ወጥተው እንግዳ
ፍለጋ የሚሄዱ ደግ ፥ ፈጣሪንና ሰውን
አክባሪ ነበሩ ።

አለቃ መዝሙር ዘዳዊት ከሕግ ባለ
ቤታቸው ከወይዘሮ ሸዋዬ ደስታ አም
ስት ልጆች ወልደው ሰላሳ የልጅ ልጆ
ች ያዩ ሲሆን ፥ በመጨረሻ በ፲፱፻፷፰
ዓ.ም በኢየሩሳሌም በዓልዓዛር ተክለ
ሃይማኖት ገዳም ሥርዓተ ምንኩስናን
ከባለቤታቸው ጋር ተቀብለዋል ። ምን
ም መልካም ሥራ ቢበዛ ሞት ለማንኛ
ውም የሰው ልጅ የማይቀር ዕጣ በመ
ሆኑ አለቃ መዝሙር ዘዳዊት በተወለዱ
ልክ በ፹፫ ዓመታቸው ሰኔ ፲፰ ቀን ፲፱፻
፸፰ ዓ.ም. ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ ።
የቀብራቸውም ሥነ ሥርዓት የዓራተ ማ
ርያም ካህናት ልብሰተክህኖአቸውን ለ
ብሰው አስከሬናቸውን በማጀብ ደብረ
ሊባኖስ ገዳም ሲደርሱ የደብረ ሊባኖስ
እና ከየአድባራቱ የመጡት ካህናት በታ
ላቅ ክብርና ሥነ ሥርዓት አቀባበል አድ
ርገውላቸው ፥ ሥርዓተ ፍትሐቱ በታላ
ቅ ማዕረግ ተፈጽሞ ብፁዕ አቡነ ማቴ
ዎስ በተገኙበት ወዳጅ ዘመድ ተሰብስ
ቦ እንባውን በማፍሰስ የመጨረሻ ስን
ብት ተደርጐላቸው የቀብራቸው ሥነ
ሥርዓት ከቀኑ በ፲ ሰዓት በደብረ ሊባኖ
ስ ገዳም ተፈጽሟል ።

አለቃ መዝሙር ዘዳዊት ምንም እን
ኳን በሕይወተ ሥጋ ከመቃብር በታች
ቢውሉም ሥራቸው ከመቃብር በላይ
ሕያው ሆኖ ስለሚታይ ትውልድ ሲያስ
ታውሳቸው ይኖራል ።

ልጃቸው እምሣለ መዝሙር

# ጻድቁ አባ ሊባኖስ

ጻድቁ አባ ሊባኖስ በሮም ሀገር ሩም
በምትባል ቀበሌ ሐምሌ ሶስት ቀን ተወ
ለደ ይህችም ቦታ ለቁስጥንጥንያ ቅርብ
ናት አባቱ አብርሃም እናቱ ንግሥት
ይባላሉ በተወለደበት ቤት አስደናቂ
የሆነ ውሃ ፈልቋል ጻድቁ በመልካም
አስተዳደግ አድጐ ሥጋዊና መንፈ
ሳዊ ትምህርትን በሚገባ ተምሮ ዲያቆን
ሆኖ በተወለደበት ደብር ቀደሰዋል
አካለ መጠን ሲያደርስ ወላጆቹ የቁስጥ
ንጥንያውን ንጉሥ ልጅ አጭተው ሲያ
ጋቡት ሙሽራይቱን ትቶ ለብቻው ያድር
ጀመር አባቱም ደንግጦ ልጄ ሆይ ምን
ሆንክ አንተ እኮ ሙሽራ ነህ ወደ ጫጉ
ላህ ተመልሰህ ሒድ ዳግመኛም ሥርዓተ
መርዓዊወመርዓትን ሳትፈጽም ወደ
ውጪ እንዳትወጣ ብሎ መከሮ ቢል
ከው ከቤቱ ውጭ በረንዳ አድሮ ተገኘ
በዚህም አባቱና እናቱ በጉዳዩ አዝነው
አዕምሮ ተነሥቶት ይሆን ? ምን አገኘው
ልጃችንን ብለው ዳግመኛ መከሩት ለጊ
ዜው እሺ ያለ መስሎ ዝም ብሎ ዋለና
ሲመሽ የሙሽራ ቤቱን ትቶ ወደአባቱ
ማደሪያ ቤት መጥቶ መልአኩ ሌሊት
በሕልሙ ሊባኖስ ሊባኖስ! ብሎ ጠርቶ
ፈጥነህ ተነሥ ትልቅ አባት ወደምትሆ
ንበት ሀገር እመራሃለሁና ተከተለኝ አት
ጠራጠር በእግዚአብሔር ፊት የምቆ
መው ገብርኤል ነኝ ብሎ እየመራ ደብ
ረ ዘይት ከሚባል ገዳም አደረሰው ሥር
ዓተ ምንኩስናን እንዲቀበል ነግሮት ተ
ሠወረ በማግስቱም አባ ጳኩሚስ ወዳለ
በት ቦታ አድርሶ አገናኘው ሁለቱም ነገ
ራተ እግዚአብሔርን እንሥተው ከተ
ጨዋወቱ በኋላ የሥርዓተ መነኮሳትን
ትምህርት በመከታተል አንድ ዓመት
ከቆየ በኋላ ማዕርገ ምንኩስናን ተቀበለ
ቀጥሎም ወደእስክንድርያ ሄዶ ማዕረገ
ቅስናንና ቁምስናን ከአቡነ ሰራብዮስ
ተቀብሎ ወደአባ ጳኩሚስ ተመለሰ አባ
ጳኩሚስም በጸጋ እግዚአብሔር ተገል
ጾለት ልጄ ሊባኖስ ሆይ ጸጋ እግዚአብ
ሔር የምታገኝበት ክፍልህ ኢትዮጵያ
ነውና ወደ ኢትዮጵያ ሒድ ሰላመ
እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ይሁን ብሎ
ባርኮ መጽሐፈ መነኮሳትንና የእጅ መስ
ቀሉን ሰጥቶ አሰናበተው ጻድቁ አባ
ሊባኖስም በመልአክ እግዚአብሔር መሪ
ነት ወደኢትዮጵያ ምድር በዓፄ አላሜዳ
መንግሥት መጨረሻ አካባቢ ተሰዓቱ
ቅዱሳን በመጡ በ፭ ዓመት መጥቶ መጀ
መሪያ ኤርትራ ውስጥ ደብረ ሲና ከተባ
ለው ቦታ በጾም በጸሎት ተወስኖ ጥቂት
ጊዜ ኖሯል ከዚያም በፈቃደ እግዚአብ
ሔር ወደ አክሱም ሒዷል በአክሱም
ጽዮን ቤተ ክርስቲያን አንድ ዓመት እንደ
ኖረ መልአክ እግዚአብሔር መጥቶ እየ
መራ በአክሱም አውራጃ በቅላ ከሚባል
ተራራ ጥግ አደረሰውና ተሠወረ ጻድቁ
አባ ሊባኖስም በበቅላ ተራራ ሥር ሰባት
ዓመት በጾም በጸሎት በስግደትና በቀ
ዊም ተወስኖ ሲኖር ዋሻ ፈልፍሎ የመነ
ኮሳት መኖሪያ ሠርቷል በጸሎቱም ከደ
ረቱ ገደል ላይ ውሃ አፍልቋል።ከዚያም
ምድረ ሠራዊ ከሚባል ቦታ ሒዶ ሲጸ
ልይ ከደረት ዋሻ ላይ ፈዋሴ ዱውያን
የሆነ ጸበል አፍልቋል በአክሱም አጠ
ገብ ምድረ በዳ በሆነ ዋሻ ተቀምጦ በጾም
በጸሎት ተወስኖ ሲኖር አንዲት ሴት
ልጅ አዝላ በገንቦ ውሃ ልትቀዳ አባ
ሊባኖስ በሚኖርበት አካባቢ ስትሔድ
አድጧት ወደቀች በዚህም ጊዜ ያዘለችው
ሕፃን ወድቆ ሞተና ታለቅስ ጀመር ጻድ
ቁ አባ ሊባኖስ ከተሠወረበት ወጥቶ
በያዘው ትምእርተ መስቀል አማትቦ
ቢጸልይ የሞተው ሕፃን ዳነ ያችም ሴት
የሞተው ልጅዋ ስለዳነላት ደስ ብሎአት
እግዚአብሔርን አመሰገነች ከጻድቁም
እግር ወድቃ ሰገደች ።

አባ ሊባኖስ የአክሱም ንቡረ እድ
ከነሹሞቹ ከንጉሡ ጋር በመሻረክ መማ
ለጃ ጉቦ ከሕዝቡ ላይ ሲቀበሉ ተገልጾ
ለት ይህንም ጉዳይ ለንጉሡና ለንቡረ
እዱ ዘርዝሮ እንደዚህ ያለ ሕገወጥ ሥራ



አትሥሩ ብሎ አስተማራቸው በዚህ
ጊዜ ንጉሡና ንቡረ እዱ ተቆጥተው በአ
ክሱም አውራጃ እንዳይቀመጥ አባረሩ
ት ጻድቁ አባ ሊባኖስም ከዚያ ምድረ
ደረቃ ወደሚባል ተራራ ጥግ ዋሻፈል
ፍሎ ለራሱና ለመነኮሳት መኖሪያ ሠርቶ
ተቀመጠ በተአምራትም ከሚጸልይበት
ቦታ የታመመ የሚፈውስ ፀበል ፈለቀ
ለት ከዚህ በኋላ አባ ሊባኖስ ከዚያ ተነ
ሥቶ ገዳመ ተረካ ወደሚባል ሔዶ ተቀ
መጠ ከዚያም በጾም በጸሎት ተወስኖ
ሲኖር ሰዎች የማይገባ የተንኮል ሥራ
እየሠሩ አስቸገሩት ጻድቁም ከቤቱ ወጥ
ቶ ተቀበላቸው እነርሱ ግን እየቀለዱ
ምክሩን አልቀበለው ስላሉ በዓቱን ለቆ
ወደሸዋ መጣና ዘጋመል ከምትባል ጥግ
ቦታ ተቀመጠ በዚህችም ዘጋመል በምት
ባል ቦታ ላይ ብዙ ውኃ በጸሎት አፈለቀ
ከብዙ ዘመን በኋላ መልአከ እግዚአብ
ሔር አባ ሊባኖስ ወደሚኖርበት መጥቶ
ይህች ቦታ የአንተ ቦታ አይደለችም ከአ
ንተ በኋላ ለሚመጣው ሰው ተውለት ስ
ለድካምህም ይህ ዘጋሜል የተባለ ቦታ
ደብረ ሊባኖስ እየተባለ እስከዘለዓለም
ይጠራልህ ብሎት ተሠወረ ከዚህ በኋላ
ከዘጋሜል ተነሥቶ ፈለገ አሸከላ ደረሰ
በዚያም ስፍራ ታቦተ ኪዳነ ምሕረት
ተገልጻለት ከተሠወረችበት አውጥቶ
ገዳም አድርጐ መካነ ገነቴ ሔዷል ከዚ
ያም ውራፍ ቁልፍ አንባ ዋሮ ላስታ
ሮሃ ገነተ ማርያም መካነ ቅዱሳን ደርሶ
የሰሙ ማስታወሻ የሚሆኑ ዋሻዎችን
አን ፏል በስሙም ጸበልን አፍልቋል
በተጨማሪም ወደበጌምድር ሄዶ አፈራ
ውናት እመደብር ዳራ ጥናፋ ሰቀልት ጀ
ናሞራ ኪና ሸዋደ በሚባሉ ልዩ ልዩ ቦ
ታዎች ለቤተ ክርስቲያን የሆኑ ተመሳ
ሳይ ዋሻዎችን አንፏል በሰሙም ጸበል
ፈልቆለታል ።

ከዚያም በአክሱም በዓድዋ በማይ
ጨው በተንቤን በአጋሜ በሁለት አው
ላሎ በአማሴን በመሳሰሉት አውራጃ
ዎች ጠቅላላ በኢትይጵያ ሰማንያ ዋሻዎ
ችንና ብዙ ጸበሎችን አፍልቋል በጸለ
የባቸው ቦታዎች ሁሉ አጋንንት ሰውን
ድል እንዳያደርጉ ቃል ኪዳን ከአ
ምላክ ተቀብለዋል ብዙ ሙት አን
ሥተዋል በአፈለቀው ውሃ ብዙ ሕሙማን
ተፈውሰዋል ሥጋውን በጾም በጸሎት
በቀዊም በሥራ አድክሟል ከሰባት
ቦታ ላይ በኢትዮጵያ አውራጃዎች የአ
ንድነት ገዳም አቋቁሞአል ብዙ ኢአማ
ንያንን አስተምሮ አጥምቋል ካህናትን
ዲያቆናትን ሹሟል በዚያም መግብ
በተባለው በዓቱም ከፈጣሪው ጋር በጸ
ሎት ተገናኝቶ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶ
ስ ለጻድቁ አባ ሊባኖስ ተገልጾ ወዳጄ
ሊባኖስ ሆይ በየክፍለ ሀገሩ ባፈለቅሃ
ቸው ጸበሎች ሁሉ የተጠመቁ በሽተኞች
ይፈወሱበታል ዓይን የሌላቸው ዓይና
ቸው ይበራል ጆሮአቸው የደነቆረ ይሰ
ማሉ ለምፅ ያለባቸው ከለምጻቸው ይፈ
ወሳሉ ። ለኃጢአተኞችይቅርታ ይደረ
ግላችዋል ።



ጻድቁ አባ ሊባኖስ

ወዳጄ ሊባኖስ ሆይ እንደወደድከኝ
ወድጄሃለሁ ስምህን የጠራ ዝክርህን
የዘከረ መታሰቢያህን ያደረገ በመቃብርህ
ቦታ የተቀበረ ስለአንተ ምሬልሃለሁ
አሥራተ ምሕረትም አድርጌ ለአንተ
ሰጥቸሃለሁ ብሎ ቃል ኪዳን ከሰጠው
በኋላ ባርኮት ከፊቱ ተሠወረ ጻድቁ አባ
ሊባኖስም ይህን የመሰለ ታላቅ የምሕረ
ት ቃል ኪዳን ስለሰጠው ለፈጣሪው ከፍ
ያለ ምስጋና አቀረበ ከዚህ በኋላ በዓፄ
ገብረመስቀል ዘመነ መንግሥት ጥር
ሶስት ቀን አርፎ ተማሮቹ ገንዘው በዚህ
በትግራይ ክፍለ ሀገር ውስጥ ገዳመ ተርካ
በሚባል ገዳም በክብር ዋሻ ፈልፍለው
ቀበሩት በመቃብሩም ላይ ፈዋሴ ዱው
ያን የሆነ ጸበል ፈለቀ በዕለተ ቀብሩ ቀስ
ተደመና በመቃብሩ ዙሪያ በሰማይ አሸብ
ርቆ ታየ ሲል ገድሉ ይናገራል ከዚህ ቀጥ
ሎም ዓፄ ገብረመስቀል በመቃብሩ ላይ
ታላቅ ቤተ ክርስቲያን አሰርቶ ምህላና
ቅዳሴ ጸሎተ ዕጣን እንዳይታጐልበት
ብሎ ብዙ ርስት ጉልትና ልዩ ልዩ መተ
ዳደሪያ ለመነኮሳቱ ሰጥቶ ገደመለት
ከዚያ ዘመን ጀምሮ በመቃብሩ አፈርና
ጸበል እየተቀቡና እየተጠመቁ የሚፈ
ወሱት ሕሙማን እጅግ ብዙ ናቸው ገዳ
ሙም ከዚያ ዘመን ጀምሮ እንደተከበረ
ነው ብዙ መናንያኝም ይገኙበታል ፥ ዛ
ሬም ያው ታምራቱን አላቋረጠም ።

ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን የዚህን ጻድ
ቅ የቅድስና ሥራ ተመልካታ ገድል
ጽፋ የተወለደበትን ሐምሌ ሦስት ቀን
ያረፈበትን ጥር ሶስት ቀን በከፍተኛ
ሥነ ሥርዓት ታከብረዋለች የዜናው
አቅራቢ አባ ገብረ መስቀል ተስፋዬ
ዘገነተ ማርያም ።



www.ethiopianorthodox.org

# ፀባቴ ገብረ ሥላሴ ወንድም አገኘሁ

ታላቁ አባት ፀባቴ ገብረ ሥላሴ ወንድም አገኘሁ በ፲፰፻፹፰ ዓ.ም. ኅዳር ፳፰ ቀን በጐንደር ክፍለ ሀገር ደብረ ታቦር አውራጃ ልዩ ስሙ ምንደጐ ተክለ ሃይማኖት ከብላታ ወንድም አገኘሁ እሸቱና ከወ/ሮ ጠይማ ወልዱ ተወለዱ ዕድሜአቸው ለትምህርት ሲደርስ በተወለዱበት ደብር ከአባ ከሃሊ ዘንድ ትምህርት ጀምረዋል ። ከዚያም ወደ ደብረ ታቦር ከተማ ሂደው ከመሪ ጌታ እንግዳ ዳዊት መዝሙርና የቃል ትምህርት ተምረው እንደፈጸሙ ወደአዛውር ኪዳነ ምሕረት ሂደው ከመሪ ጌታ ገብረ ኢየሱስ ጾመ ድጓ ምዕራፍ ተምረው እንደ ፈጸሙ ከአቡነ ጴጥሮስ ዲቁና ተቀብለው ወደተወለዱበት ደብር ምንደጐ ተክለ ሃይማኖት ተመልሰው እየቀደሱ ቅኔ ከመሪጌታ ድንቄ ተምረዋል ከዚያም ወደ ገንተኛ ማርያም ሔደው ከአባ እንግዳ ወርቅ ዘንድ ቁም ጽሕፈትና መዝገብ ቅዳሴ በሚገባ ተምረው በቅዳሴ መምህርነት ከተመረቁ በኋላ በሥርዓተ ተክሊል ሚስት አግብተው አንድ ወንድ ሁለት ሴቶች ልጆችን ወለዱ የቅስና ሲመትን ከአቡነ ማቴዎስ ተቀብለዋል በቅስና ቤተ ክርስቲያን አገልግለዋል ። በኋላም ሚስታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ስለተለዩባቸው ወንዱን ልጃቸውን አስከትለው ወደሰይኮ ገዳም ኪዳነ ምሕረት ሒደው ሥርዓተ ምንኩስናን ተምረው የምንኩስና ማዕርግን ተቀብለው ወደደብረ ታቦር መድኃኔ ዓለም በመሄድ ከታወቁት ሊቅ ከሐዲስ ተክሌ የአርባዕቱ ወንጌላትን ትርጓሜና ፍትሐ ነገሥት ባሕረ ሐሳብ አጠናቀው ተምረዋል ።

ከዚያም በኋላ የዚሁ አውራጃ አስተዳዳሪ ለነበሩት ለፊታውራሪ አስፋው መምህረ ንስሃና አማካሪ እንዲሆኑ ተመርጠው ከአስተዳዳሪው ጋር አብረው ተቀምጠው መንፈሳዊውንና ሥጋዊውን ትምህርት በአመች ሰዓት እያስተማሩ ፬ (አራት) ዓመት ያህል እንደ ቆዩ በፈቃደ እግዚአብሔር በ፲፱፻፲፯ ዓ.ም. ላይ ከጐንደር ወደ አዲስ አበባ መጥተው ከንግሥት ዘውዲቱ ምኒልክ ጋር ተዋውቀው በጐንደር ክፍላተ ሀገር ለሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት አስታዋሽ እንዲሆኑ ተመደቡ ከዚህም ሌላ በተጨማሪም የቁምስና ማዕርግ ከአቡነ ማቴዎስ ዘንድ ተቀብለው ደብረ



ፀባቴ ገብረ ሥላሴ ወንድምአገኘሁ

ታቦር መድኃኔ ዓለምን መቅደስ ማርያምን ፣ እናቲቱ ማርያምን ፣ ጣና ቂርቆስን ፣ ክርስቶስ ሠምራን ፣ ደብረ ማርያምን እማ ወተት ጊዮርጊስን ፣ ጐንድ ተክለ ሃይማኖትን ፣ ቃናት ተክለ ሃይማኖትን ተሹመው ለብዙ ዘመን አስተዳድረዋል ። ጠቅላላ በጐንደር ክፍለ ሀገር ለሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት ለንግሥት ዘውዲቱ ምኒልክ እያሳሰቡ ብዙ ንዋየ ቅድሳትን አድለዋል ።

የእናቲቱ ማርያምንና የቃናት ተክለ ሃይማኖትን የሊማደ ማርያምን አብያተ ክርስቲያናት ከዳን ለውጠው ቆርቆሮ አስከድነዋቸዋል ።

ከዚያም ልዑል ራስ ካሣ ኃይሉ የጸባቴ ገ ሥላሴን መልካም ዝና ሰምተው ከርሳቸው ጋር ሁነው በሐሳብና በምክር አባት እንዲሆኗቸው ተጠይቀው ፈቃደኛ በመሆናቸው ከልዑል ራስ ካሣ ጋር አዲስ አበባ ከተማ እንጦጦ ገነተ ኢየሱስ ተቀምጠው የራስ ካሣ የንስሐ አባትና አማካሪ ሁነው እንደተቀመጡ የደብረ ሊባኖስ ገዳም አስተዳዳሪ በመሆን ፀባቴ ተብለዋል ። ከዚያም በወሎ ክፍለ ሀገር የላስታ አውራጃ አስተዳዳሪ ለነበሩት የራስ ካሣ ልጅ ወንድወሰን አማካሪና ሞግዚት ሁነው በተጨማሪ የገነተ ማርያም ደብር አስተዳዳሪ በመሆን ተሹመው ሒደዋል ። የገነተ ማርያምን ደብር በተሾሙበት ዘመን የዓፄ ይኩኖ አምላክን ገድልን አጽፈው ለገነተ ማርያም ደብር ሰጥተዋል ። ከዚህ ሌላ በላስታ አውራጃ ውስጥ ለሚገኙት የጊስ አንባ ማርያም የጠፍለጢት ማርያም የጩህና ጊዮርጊስ የውሃ አቦ ገብረ መንፈስ ቅዱስ አድባራት መምህር ከመሆናቸውም በላይ የላስታ አውራጃ ሊቀ ካህናት ሁነው አስተዳድረዋል ከዚያም የየጁ አውራጃ ቤተ ክህነት ኃላፊ ሁነው ሠርተዋል ። ከዚያም የወሎ ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ ሁነው ሠርተዋል ። ከዚያም ተመልሰው ሁለተኛ ለልዑል ራስ ካሣ አማካሪ በመሆን ወደጐንደር ሔደው ሠርተዋል ። ከዚያም ተመልሰው ዳግመኛ ሁለተኛ የፍቼ ጊዮርጊስ ደብርና የደብረ ሊባኖስ ገዳም አስተዳዳሪ ሁነው ብዙ ቁም ነገሮችን በገዳሙና በደብሩ አቋቁመዋል ። ኢጣልያ ፋሽሽት በመጣ ጊዜ ማይጨው ዘምተዋል በኢጣልያ ፋሽስት እጅም ፭ ዓመታት ታሥረዋል ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የይግባኝ ሰሚ መንፈሳዊ ዳኛም ሁነው ሠርተዋል ።

ከዚያም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ጉባኤ ሰብሳቢ ዳኛና የገነተ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ ሁነው ብዙ ዘመን በታማኝነትና በቅንነት ቤተ ክርስቲያንን ካገለገሉ በኋላ የጡረታ ዘመናቸው ስለደረሰ የጡረታ መብታቸው ተጠብቆላቸው በጾምና በጸሎት ተወስነው በገነተ ኢየሱስ መኖሪያ ቤታቸው በሕይወት ይገኛሉ ። የአርበኝነት የወርቅ ሜዳይ ተሸልመዋል ። ከቤተ ክህነት የምስክር ወረቀትና ሽልማት አግኝተዋል ።

እኒህ ታላቅ አባት ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከ፶ ዓመት በላይ በሥራ ምድባቸው ብዙ ቁም ነገር ያለው ሥራ ሠርተዋል ። በእስክንድርያና በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መካከል ስለ ነበረው በኢየሩሳሌም ገዳም ጉዳይ ስምምነት እንዲፈጠር በኢትዮጵያ በኩል ተወክለው ወደ ኢየሩሳሌም ሔደው ጉዳዩ በሰላም እንዲፈታ አድርገዋል ። ስለኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት አስተዳደር ጉዳይም የቤተ ክህነት አፈ ጉባዔ ሁነው ለመንግሥት ጥያቄ አቅርበው ጥያቄያቸው ተቃንቶ በሥራ ላይ ውሏል ። በቤተ ክህነት አጠቃላይ ስብሰባ በሚደረግበት ጊዜም አሳባቸው ተቀባይነት ነበረው ታላቁ አባት ፀባቴ ገብረ ሥላሴ እንደበተ ርቱዕ ድምፀ መልካም የንባብ ችሎታ ያላቸ ስለሆኑ ደብረ ሊባኖስ ገዳምና በሌሎቹም ታላላቅ ገዳማትና አድባራት በዓመት በዓል ቅዳሴ እንዲቀድሱ የሚጋበዙት እርሳቸው ነበሩ ጸባቴ ገብረ ሥላሴ ጨዋታቸው የማይጠገብ ታላቅ አባትናቸው ። እኒህ ታላቅ አባት አሁን ዕድሜያቸው ሰማንያ ዘጠኝ ዓመት ሲሆን በሰላም ይገኛሉ ወደቤታቸውም ሂዶ ለሚያወያያቸው ሰው ጠቃሚ ምክርን ይሰጣሉ እኒህ ታላቅ አባት ዛሬ ዓይናቸውና ጉልበታቸው ደክሞ ከቤት ቢውሉም በጾምና በጸሎት ተወስነው ለሀገርና ለወገን ሰላምን በመለመን ላይ ይገኛሉ ። ጊዜውን መሥዋዕት አድርጐ ሂዶ ከርሳቸው ጋር የሚወያይና የሚጫወት ሰው ብዙ ነገሮችን ለመቅሰም ይችላል ።

ፀባቴ ገብረ ሥላሴ ከአስተዳደርም ከዕድሜም ብዙ ተምረው ያወቁ ስለሆኑ በምክራቸው ለመጠቀም ይቻላል ። ምክንያቱም ፀባቴ ገብረ ሥላሴ ወንድም አገኘሁ ዛሬ በሕይወት ቢገኙ ነገ የማይገኙ ስለሆኑ ለቀሪ ትውልድ ታሪክ ለማስቀረት ወደ እርሳቸው ሂዶ መጠየቅና ከእርሳቸውም ጋር መወያየት ታላቅ ብፁህነት ነው ።

አባ ገብረ መስቀል ተስፋዬ ።



# ጴጥሮስ ወጳውሎስ

በመጀመሪያው አምድ የቅዱስ ጴጥሮስን ታሪክ አስቀድማለሁ ።

ጴጥሮስ ማለት በመተርጉማን እንደ ተገለጠው አለት ማለት ነው ። ይህንም የቀን ሐሩር የሌሊት ቁር አይለውጠውም ቅዱስ ጴጥሮስ መንፈስ ቅዱስን ከተቀበለ በኋላ በመከራ አለተለወጠምና ።

የሃይማኖት መሠረት ሆኖአል ። ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኔ መሠረት ነህ ብዬ እነግርሃለሁ ብሎ መስክሮለታል ።

መሠረትነቱም የትምህርት ነው በቅዱስ ጴጥሮስ ሃይማኖትና ትምህርት የታነፁ ምዕመናንን መናፍቃንና አጋንንት በክህደትና በስህተት ድል እንደ ማይነሷቸው ተገልጦአል ።

በሌላ በኩልም የቅዱስ ጴጥሮስ የትውልድ ሀገሩ ከገሊላ ባሕር ዳር ቤተ ሣይዳ ይባላል ። የአባቱ ስም ዮና ነው ትውልዱ ከነገደ ሮቤል ነው እናቱም ከነገደ ስምዖን እንደነበረች ይናገራል ። በእናቱ ነገድ ስምዖን ተብሎአል ። ስምዖን ማለትም እግዚአብሔር ሰማኝ ማለት ነው ።

አምስት ዓመት ሲሆነው ቅፍርናሆም በተባለው ሀገር ሕገ ኦሪትን እየተማረ አደገ ። ዓሣ እየጠመደ እየሸጠ ሲጠቀም ይኖር ነበር ። እንደዚህም እያደረገ ሲኖር እግዚአብሔር በነቢያት የተነገረውን ለመፈጸም ሰው ሆኖ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወለደ በእየጥቂቱካደገ በኋላ በ፴ ዓመቱ በዮሐንስ እጅ ተጠምቆ ፵ ቀን ጾሟል መዋዕለ ጾሙን ሲፈጽም በገሊላ ባሕር ማዶ ሲመላለስ ወንድማማቾችን አገኘ እነሱም ስምዖን የተባለ ጴጥሮስና እንድርያስ ናቸው እነርሱንም ዓሣ ሲአጠምዱ አገኛቸውና ተከተሉኝ አላቸው ለጊዜው በእግር እንዲከተሉት ነው ።

ምሥጢሩ ግን መከራ መስቀልን በመቀበልና በማስተማር ምሰሉኝ ማለቱ እንደሆነ ተገልጦአል ። እንግዲህ ሰውን እንደ ዓሣ ወንጌልን እንደ ወጥመድ ይህን ዓለም እንደ ባሕር አድርጋችሁ እንድታስተምሩ አደርጋለሁ ብሎ አቻቸዋል ። እነሱም በመረጣቸው ጊዜ ሁሉን ትተው ተከትለውት ሄደዋል።

እንግዲህ ቅዱስ ጴጥሮስ በሐዋርያነት ከተመረጠበት ቀን ጀምሮ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ተከትሎ ትምህርተ ወንጌልን እየተማረና አስደናቂ የሆነ ተአምራቱን እያየ ፫ ዓመታት ከሦስት ወራት አብሮ እንደኖረ ታውቋል ።

ጌታችን ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ አስቀድሞ ለጴጥሮስ እንደ ተገለጠለትና በ፴፱ኛው ቀንም አስቀድሞ እንደሚወደው ከጠየቀው በኋላ በጎቼን ጠብቅ ብሎ የማስተማር ኃላፊነትን አስረከቦታል ።

ይህንንም ምዕመናንን የማስተማር አደራ ከተረከበበት ጊዜ ጀምሮ በተናሽ እስያ እየዞረ ወንጌልን በቃል ከማስተማሩም ሌላ መልክትም እየጻፈ ይልካቸው እንደ ነበረ ይተረካል ያስተማራቸው ምእመናን በሃይማኖት እንዲፀኑ ይመክራቸው ነበረ ያለ መከራ ክብር አይገኝምና መከራውን እንዲታገሡ ያጽናናቸው ነበር ።

እንግዲህ የቅዱስ ጴጥሮስን ታሪክ



www.ethiopianorthodox.org

በዚህ ዓምድ ተንትኖ ለማቅረብ የሚ በዛ ስለሆነ አጠር በማድረግ ሐምሌ ፭ ቀን የሚከበረውን ዜናሞቱን እገል ጻለሁ ።

በ፷ ዓመተ ምሕረት ወደ ሮም ገብቶ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እየመሰከረ በማ ስተማር ላይ ሳለ ኔሮን ቄሣር በዚያን ዘመን በክርስቲያኖች ላይ ቁጣው ይቃ ጠል ስለነበረ ቅዱስ ጴጥሮስን አስይዞ እንዲታሰር አደረገ ምክንያቱ አረማው ያንን ደስ ለማሰኘትና አምልኮ ጣዖት እንዲሰፋ ለማድረግና ትምህርተ ወን ጌል እንዲጠፋ ነበር ግን በእግዚአብ ሔር ቸርነት አልጠፋም ። የቅዱስ ጴጥ ሮስም ሞት በመስቀል እንዲሆን ትእ ዛዝ ተሰጠ የሚሰቀልበት ሰዓት በደረሰ ጊዜ ከእሥር ቤት አውጥተው ሲወስ ዱት አንድ ነገር እንዲአደርጉለት ጠየ ቃቸው ።

ይህም ትሕትናንን የሚመለከት ነ በረ ከጌታዬ ከኢየሱስ ክርስቶስ ዕኩል እንዳልሆን ራሴን ወደታች ዘቅዝቃ ችሁ ስቀሉኝ ብሎ ለመናቸው ። ሐምሌ ፭ ቀን ፷ ዓመተ ምሕረት ዝቅዝቅ ተሰ ቅሎ በመሞቱ ከፈጣሪው የተነገረውን ሐዋርያዊ ግዴታውን ፈጽሞአል ። አስ ቀድሞ ከአምልኮተ እግዚአብሔር ባ ዕድ የሆነ ኔሮን ቄሣር በመስቀል አሰ ቅሎ እንዲገድለው ነግሮት ነበርና ። ቅዱስ ጴጥሮስም መከራ መስቀልን በመቀበሉ አላዘነም ነበር በማስተማ ርም ሆነ መከራ መስቀልን በመቀበል ፈጣሪው ኢየሱስ ክርስቶስን መስሎ ታልና ።

እንግዲህ ከፈጣሪው የተሰጠውን የማስተማርና የሃይማኖት አደራ ከአስ ረከበ በኋላ በተአማኝነቱ የመንግሥተ ሰማያትን መክፈቻ ለመረከብ ችሎ አል ።

መክፈቻ የተባለውም የብረት ቁልፍ ሳይሆን ወደ መንግሥተ ሰማያት የማስ ገባትና ያለማስገባት ሥልጣነ ክህነት እንደሆነ እንመለከታለን ።

እንግዲህ ቅዱስ ጴጥሮስን በሥራ ከመሰለው በክብርም እንድንመስለው አጠራጣሪ አይሆንም ።

በሌላ በኩልም ከላይ በርእሱ እንደተ ገለጠው ቅዱስ ጴጥሮስን አስቀድሜ በተከታታይ የቅዱስ ጳውሎስን ሐምሌ ፭ ቀን የሚከበረውን በዓል መታሰቢያ በማድረግ በመጠኑ እገልጣለሁ ።

ቅዱስ ጳውሎስ የመጀመሪያ ስሙ ሳውል ነበር ይህም ሀብተ እግዚአብ ሔር ማለት ነው የትውልድ ሀገሩ ጠር ሴስ ይባላል የኪልቅያ የባህር ጠረፍ ከተማ ነው ። እድሜው ፲፭ ዓመት ሲሆን በኢየሩሳሌም ከታላቁ መምሕር ገማልያል ሕገ ኦሪትን ተምሮ ነበር ገማ ልያል ፈሪሳዊ ስለነበረ ቅዱስ ጳውሎ ስም ከእርሱ በመማሩ ለሕገ ኦሪት ቀና ተኛ ሆኖ ነበር ቀናተኛ ማለትም ከራሱ ሃይማኖትና ሕግ በቀር ሌላ ሃይማኖትና ሕግ ያለ አይመስለውም ነበር ስለዚህ የሌላውን ሃይማኖትና ሕግ የማይቀ በል ማለት ነው ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በኢየሩሳ ሌም በአስተማረበት ዘመን (ጳውሎስ በኢየሩሳሌም አልነበረም ግን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሰማይ በዓረገ በ፷ ዓመት ጳውሎስ ምዕመናንን ለማ ሠር የሹመት ደብዳቤ ከሊቀ ካህናቱ ተቀብሎ ወደ ደማስቆ ሲሄድ ከከተ ማው ለመግባት ጥቂት ሲቀረው በድን ገት የሰማይ ብርሃን በላዩ ላይ አበራ በት ።

ይህም ብርሃን ጌታችን ኢየሱስ ክር ስቶስ ለጳውሎስ ሲገለጥለት የክብሩ ብርሃን ነው ጳውሎስም ከድንጋጼው የተነሣ በምድር ላይ ወድቆ ነበር ወዲ ያውም ሳውል ሳውል ለምን ታሳድደ ኛለህ የሚል ድምፅ ሰማና አንተ ማነህ ብሎ ቢጠይቅ አንተ የምታሳ ድደኝ የናዝሬቱ ኢየሱስ ነኝ ካለ በኋላ በሹል ምስማር ላይ ብትረግጥ ላንተ ይብስሐል አለው ይህም አባባል ፈጣሪ ህን ብትከድ አንተ ትጎዳለህ ማለቱ እንደሆነ እንገነዘባለን ። ጳውሎስም እየተንቀጠቀጠ አቤቱ ምን አደርግ ዘንድ ትሻለህ ብሎ ቢጠይቀው ወደ ከተማ በገባህ ጊዜ ልታደርገው የሚገባ ህን በዚያ ትሰማለህ አለው ።

ቅ/ጳውሎስም ዓይኖቹ ተገልጠው ሳሉ ከድንጋጤው የተነሣ ምንም አያ ዩም ነበርና ከእርሱ የነበሩ እየመሩ ወደ ደማስቆ አድርሰውታል በደማስ ቆም ሐናንያ የሚባል በክርስቶስ ያመነ ሰው ነበረ ። ለእርሱ ጌታችን በዕራይ ተገልጦ ስለ ጳውሎስ አነጋገረው ለአ ሕዛብና ለእስራኤል ልጆች በስሜ እን ዲያስተምር ምርጥ ዕቃ አድርጌዋለሁ ብሎ ለሐናንያ ከነገረው በኋላ ሐናን ያም እጁን ጫነበትና አጠመቀው በ ዚያ የዓሣ ግልፋፊ የመሰለ ከዓይኖቹ ተገፎ ወደ ቀለትና ብርሃን አየ ።

እንግዲህ ከተጠመቀ በኋላ ዓይነ ሥጋው ብቻ ሳይሆን ዓይነ ልቡናውም በመንፈስ ቅዱስ ብሩህ እንደሆነለትና በክርስቶስ እንደ አመነ እንገነዘባለን።

ከዚህ በኋላ ስለ ክርስቶስ እየመሰከረ የእግዚአብሔርን መንግሥት በመስ በኩ ከአሕዛብ ወገን ብዙዎችን ከአም ልኮተ ጣዖት ወደ አምልኮተ እግዚአብ ሔር ከገቢረ ኃጢአት ወደ ገቢረ ጽድቅ መልሶአቸዋል ።

እንግዲህ ጳውሎስ ማለት ምርጥ ዕቃ ማለት ነው ይህም መዶሻ ማለት ነው መዶሻ ጂቱን መአድናት ቀጥቅጦ አንድ ያደርጋል ሰባቱ ማድናትም ወር ቅ ብረታብረት መዳብ ናስ ወዘተ ና ቸው እሱም እስከ ተፍጻሜተ ምድር በባሕርና በየብስ እየተጓዘ አረማውያ ንን አስተምሮና አሳምኖ አጥምቆ ከአ ምልኮተ ባዕድ ነፃ አውጥቶ የክርስቶስ ተከታዮች አድርጎአቸዋል ።

ሲአስተምርም በቃል ብቻ ሳይሆን ፲፬ መልከታት ጽፎላቸው እንደነበረ ይታወሳል መልከታቱም ለምዕመናን የሚአረካና የሚጥም ትምሕርት ከመስ ጠታቸውም ሌላ ለሃይማኖትና ለሥነ ምግባር መልካም መመሪያ ሆነው ይገ ኛሉ ።

እንግዲህ ቅዱስ ጳውሎስ ከማስተማ ርና ከእጅ ሥራ የአረፈበት ጊዜ ከቶ አልነበረም በእሥር ቤት ሆኖም ያስተ ምር እንደ ነበር ይተረካል ። በሰማዕት



# “ሕሙማንን ሁሉ እንዲፈውሱ ሥልጣንን ሰጣቸው”


ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክር ስቶስ ሰው ሆኖ ሥጋን ለብሶ በዚህ ዓለ ም ፴ ዓመት ከኖረ በኋላ በማየ ዮርዳኖ ስ ተጠምቆ ሲያበቃ ወደ ገዳም ሄዶ ፵ ቀንና ሌሊት ከጾመ በኋላ ደቀ መዛሙ ርቱን መርጦ ወንጌልን አስተምሯቸ ዋል ።

ለደቀ መዛሙርቱ ባስተማረው ትም ህርት የማቴ. ወን. ፲፥፩ አሥራ ሁለቱን ሐዋርያት ወደ እርሱ ጠርቶ እንዲያወ ጧቸው በርኩሳን መናፍስት ላይ ደዌን ና ሕሙማንንም ሁሉ እንዲፈውሱ ሥልጣንን ሰጣቸው ድውዮችን ፈውሱ ሙታንን አንሡ ለምጻሞችን አንጹ አጋ ንንትን አውጡ ይላል ።

በተጨማሪም ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ ለአ መኑት እነዚህ ተአምራት ይደረጉላቸዋ ል በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ እባቦችን ይይዛሉ የሚ ገድልም መርዝ ቢጠጡ አይጐዳቸው ም እጃቸውን በድውዮች ላይ ይጭናሉ እነርሱም ይድናሉ በማለት አስተምሯ ቸዋል ማርቆስ ፲፮፥፲፭ ።

ደቀ መዛሙርቱም ይህንን የጌታችን

ይህንንም ወንጌላዊው ሉቃስ ሲገልጽ በሐዋርያትም እጅ ብዙ ተአምርና አስ ደናቂ የሆኑ ሥራዎች ይፈጸሙ ነበር ስ ለዚህ ጴጥሮስ ሲያልፍ ጥላውም ቢሆን ከበሽተኞች ላይ ሲያርፍ በሽተኞችን ወደ አደባባይ አውጥተው በአልጋ ላይ



መ/ ወልደ ትንሣኤ ይግዛው

ን የኢየሱስ ክርስቶስን ቃል መሠረት በማድረግ ዓለምን እየዞሩ ባስተማሩበ ት ወቅት ድውያነ ሥጋን በተአምራት ድውያነ ነፍስን በትምህርት አድነዋል

ያኖሯቸው ነበር ደግሞም በኢየሩሳሌ ም ዙሪያ ካሉችው ከተማ ድውያንና በር ኩሳን መናፍስት ተይዘው የሚሠቃዩት ን እያመጡ በሐዋርያት አጠገብ ያስቀ

ነት በሚሞትበት ጊዜ ደቀ መዝሙሩ ጢሞቴዎስ ሊጠይቀው መጥቶ ሳለ የመ ሰነባበቻ ንግግር አድርጐለት ነበር ቃሉም ይህ ነው መልካሙን ገድል ተጋደልሁ ሩጫዬንም ጨረስሁ ሃይማ ኖቴንም ጠበቅሁ ከእንግዲህ ወዲህ ግን እግዚአብሔር የሚሰጠኝ የጽድቅ አክሊል ይቆየኛል ብሎአል ።

ከዚህም በኋላ ሐምሌ ፭ ቀን ፷ ዓ መተ ምህረት በሮም የነበረ ኔሮን ቄሣር በሰይፍ አንገቱን አስቆርጦት በሰማዕትነት ሞቷአል እንግዲህ ቅዱስ ጳውሎስ በሃይማኖቱና በስነ ግብሩ ተወዳዳሪ የማይገኝለት የዘለዓለም ክ ብር አግኝቶአል ።

እኛም ምዕመናን የቅዱስ ጳውሎስን አሠረ ሃይማኖትና ሥነ ምግባር ከተከ ተልን ለእሱ የተሰጠው የጽድቅ አክ ሊል ለእኛም እንዲቆየን በእምነት ተስፋ እናደርጋለን ለዚህም የእግዚአ ብሔር ፈቃዱ ይሁንልን አሜን ።

መምህር ኪዳነ ማርያም አየለ



www.ethiopianorthodox.org

ረስ በጠቅላይ ቤተ ክህነት በመንፈሳዊ አገልግሎት መምሪያ የበዓል አከባበር ፕሮግራም አስከባሪና ፪ኛ/ ደረጃ አጋፋሪ ሆነው ሠርተዋል ።

፮ኛ/ በ፲፱፻፷ ዓ.ም የአገልግሎት ኒሻን ከመንግሥት ተሸልመዋል ።

፯ኛ/ በ፲፱፻፷፫ ዓ.ም ከሩማንያ ፓትርያርክ ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጁስትንያን የወርቅ የአንገት መስቀል ተሸልመዋል ።

፰ኛ/ በ፲፱፻፷፭ ዓ.ም. ከሩስያ ሊቀ ጳጳስ የወርቅ መስቀል ተሸልመዋል ።

፱ኛ/ ከ፲፱፻፷ እስከ ፲፱፻፷፱ ዓ.ም. ድረስ የመንፈሳዊ አገልግሎት መምሪያ ዋና ጸሐፊ ሆነው ሠርተዋል ።

፲ኛ/ ከ፲፱፻፷፱ እስከ ፲፱፻፸፯ ዓ.ም. ድረስ ምክትል መጋቤ ካህናት ሆነው በትጋትና በንቃት አገልግለዋል በ፲፱፻፸፪ ዓ.ም. በያዙት የም/መጋቤ ካህናት ሥራ ላይ መልአከ ምሕረት መዓዛ ተብለው ተሹመው የቦሌ ደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያንን አስተዳድረዋል ።

፲፩ኛ/ ከ፲፱፻፸፯ ዓ.ም ከጥቅምት ወር ጀምሮ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፈቃድ የመጋቤ ካህናትነት ሹመት ተሰጥቷቸው በጠቅላይ ቤተ ክህነት የካህናት አስተዳደር መምሪያ ኃላፊ ሆነው እስከ ሕይወተ ሥጋቸው ፍጻሜ ድረስ በታማኝነትና በቅንነት አገልግለዋል ።

መጋቤ ካህናት መዓዛ ወ/ኢየሱስ የሰባት ወንዶች የአራት ሴቶች በድምሩ የ፲፩ ልጆች አባት ናቸው መጋቤ ካህናት መዓዛ ወ/ኢየሱስ ደግና ትሑት ርኅሩኅና ቅን ታላላቆችን እንደ አባትና እናት ታናናሾችን እንደ እህትና ወንድም የሚወዱ ነበሩ ።

መጋቤ ካህናት መዓዛ ወ/ኢየሱስ በትልቁም በትንሹም ዘንድ ተወዳጅነት የነበራቸው ደግ ካህን ነበሩ መጋቤ ካህናት መዓዛ ወ/ኢየሱስ ፴፰ ዓመት ሙሉ ሌት ከቀን ያለምንም ዕረፍት ቤተ ክርስቲያንን በቅዳሴ በሰዓታት በማኅሌት ከማገልገላቸውም ሌላ በቢሮም ሥራ ተመድበው ቤተ ክርስቲያንን ሲያገለግሉ ኑረው በተወለዱ በ፷ ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል ።

ሞት ለማንኛውም ሰው የማይቀር ዕዳ ቢሆንም መጋቤ ካህናት መዓዛ ከዚህ ዓለም በሞት መለየታቸው ኃዘኑና ጉዳቱ ለቤተ ሰቦቻቸው ብቻ ሳይሆን ለቤተ ክርስቲያናችንም ጭምር ነው ።

እግዚአብሔር አምላክ ለመጀመሪያው ሰው አዳም መሬት ነህና ወደ መሬት ትመለሳለህ ባለው ቃል መሠረት ሥጋ የለበሰ ሁሉ ከፈጣሪው የተወሰነለት ዕድሜ ሲፈጸም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቶ ወደ ዘለዓለማዊ ዕረፍት ይሄዳል ።

ነገር ግን በዚህ ዓለመ ሥጋ በሚኖርበት ወቅት የሠራው መልካም ሥራ ለዘለዓለም ስሙን ሲያስጠራው ይኖራል ሞት በተለያዩ መንገዶች ሊደርስ ይችላል ዋናው ቁም ነገር ግን በሚኖሩበት ዘመን መልካም ሥራ መሥራት ነው ።

መጋቤ ካህናት መዓዛ ወ/ኢየሱስ ከዚህ ዓለም በሞት ቢለዩም መልካም ሥራቸው የማይሞት ስለሆነ ለሁልጊዜ ሲያስጠራቸው ይኖራል ። ስለዚህ ለቤተ ሰቦቻቸው መጽናናትን ለነፍሳቸው ዘለዓለማዊ ድኅነትን እንዲሰጥ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ወደ እግዚአብሔር ትጸልያለች ።

ሊቀ ካህናት ክፍሌ ገብረ መስቀል

የቁጥጥር ክፍል ኃላፊ

## እንግዶችን መቀበል ....

ከገጽ ፯ የዞረ

ስቶስ ሁለተኛ ሲመጣ ዓለም ሳይፈጠር የተዘጋጀውን መንግሥት ለማያት የሚያወርሳቸው እንግዶችን ተቀብለው ያበሉትን ያለበሱትን ነውና እንግዶችን ለመቀበል እንሽቀዳደም ።

ቂ. ልሣነወርቅ በዛብህ

## የአለን ቅዱስ ......

ከገጽ ፳፱ የዞረ

፰ኛ/ አቶ ብርሃኔ ገለታ ፩፻
፱ኛ/ አቶ ነገራ በየነ ፩፻

የረዱ ሲሆን የቀሩት በጎ አድራጊዎች ደግሞ ከብር ፩ - ፻፶ ረድተዋል ካሉ በኋላ ሁሉንም ለመዘርዘር ጊዜን ስለሚያባክን ለዚህ ቤተ ክርስቲያን ሕንፃ በጉልበት ላገለገለ በገንዘብ ለረዳ ሁሉ እግዚአብሔር ዋጋውን ይክፈለው ብለዋል ። ባላምበራስ አድማሱ ጥሩነህ ማብራሪያቸውን በመቀጠል ለዚሁ ቤተ ክርስቲያን ማሠሪያ የወጣው ገንዘብ ብር ፺፰ሺ ፩፻፲ ከ፶፭ ሳንቲም መሆኑን ገልጸው ንግግራቸውን አጠቃለዋል ።

ይህ ቤተ ክርስቲያን በ፲፱፻፴፪ ዓ.ም ሲተከል የነበረውን ቤተ ክርስቲያን ጠላት ሠርቶ ሲገለገልበት ቆይቶ የለቀቀው ቤት ስለነበር የቦታው አቀማመጥ በቤተ ክርስቲያን ፕላን የተሠራ አልነበረም ።

ይልቁንም የተሠራው በጭቃና በእንጨት ስለነበር በጊዜ ብዛት በደረሰበት መሰንጠቅ ሊወድቅ የተቃረበ ሆኖ ይታይ ነበር ። ነገር ግን የቤተ ክርስቲያንን ሕይወት እንደራሳቸው ሕይወት አድርገው የሚመለከቱት ወገኖች ይህንን ያህል ገንዘብ በሕብረት አዋጥተው በአጭር ጊዜ ውስጥ ተሠርቶ ታቦቱ ከመቃኞ ወደተሠራው ቤተ ክርስቲያን እንዲገባ ማድረጋቸው እጅግ በጣም የሚያስደስት ነው ።

በይበልጥ በሕዝበ ክርስቲያኑ የተመረጡት ኮሚቴዎችና የኮሚቴዎቹ ሊቀ መንበር ባለምበራስ አድማሱ ጥሩነህ የግል ሥራቸውን በመተው በገንዘብ አሰባሰብ ፤ ሕዝቡን በማስተባበር በጉልበት ካደረጉት ከፍተኛ ድካም ሌላ ከግል ገንዘባቸው የከፈሉት አስተዋጽኦ ከፍ ያለ በመሆኑ ምስጋና ይገባቸዋል ።

ከፋ ሀ/ ስብከት

ጅማ ከተማ

የአለን ቅዱስ ጊዮርጊስ ሰበካ ጉባኤ

ጽ/ ቤት



# የግብርና በረከት

በዛሬው የግብርና በረከት ዓምዳችን የምናቀርብላችሁ ትምህርት አዲስ ሳይሆን ያው እንደተለመደው ዜና ግብርና ተብሎ ከተሰየመው ዝግጅት ቅጽ ፮ ቁጥር ፩ ከታህሣሥ -ጥር ፲፱፻፸፯ ዓ.ም ገጽ ፳፱ ላይ ከሠፈረው በመነሣት ነው።

ርእሱ የኅብረት ሥራ እንቅስቃሴ ብሎ ይጀምርና የሚከተለውን አስፍሯል ።

### ጐንደር ክፍለ ሀገር

በጐንደር ክፍለ ሀገር በጋይንት አውራጃ በላይ ጋይንት ወረዳ የሚገኘው የመኳቢያ የገበሬዎች አምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበር በ፲፱፻፸፫ ዓ.ም በ፳፰ አባላት ተመሥርቶ በአሁኑ ጊዜ ጥራትና ዕድገትን በሚገባ በማሳየቱ የአባላቱ ብዛት ወደ ፺፩ ከፍ ሊል ችሏል ።

ማኅበሩ ሲመሠረት መነሻ ካፒታሉ ብር ፳ ሺ ፩ መቶ ፳ ፡ ሲሆን በአሁኑ ወቅት ብር ፩ መቶ ፴፩ ሺ ፩ መቶ ፵ ከ፶ ሣንቲም መድረሱን የማኅበሩ ሊቀ መንበር ጓድ ፀዳሉ ያለው ገልጠዋል ።

ማኅበሩ ለእርሻ የሚጠቀምበት የመሬት ስፋት በሄክታር ፺፩ ነጥብ ፳፩ ሲሆን ለግጦሽ ፳፫ ሄክታር ፤ ለጓሮ አትክልት ፲ ሄክታር ለደን ደግሞ ፪ ነጥብ ፭ ሄክታር ከልሏል በዚህ በያዝነው ዓመት የማኅበሩ ምርት ከአለፈው ዓመት በጣም የቀነሰ ሆኗል ። ይህም የሆነበት ምክንያት በዝናም ዕጥረት ፤ በፀረ ሰብል ተባዮችና እንዲሁም በዚያ አካባቢ ሰብልን በከፍተኛ ደረጃ የሚያጠፋ የአይጥ መንጋ በመኖሩ ነው ።

በሌላ በኩል ደግሞ ማኅበሩ ጽሕፈት ቤትና መጋዘን (ከጉልበት ውጭ ሌላ ብር ፳ ሺ በማሠራት እንዲሁም የከብቶች መኖሪያ አዘጋጅቶ ፺፮ በሬዎች ለገበሬዎች በማርባት ላይ ይገኛል ።

የመኳቢያ አምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበር አባላት አብዛኛውን ጊዜ ለእርሻ የሚጠቀሙባቸው ፈረሶች ናቸው ። ምክንያቱም በዚህ አካባቢ ብዙ ጊዜ የበሬዎች እጥረት በመኖሩና ፈረሶች ከበሬ የበለጠ የማረስ ኃይልና ፍጥነት ስላላቸው መሆኑ ታውቋል ።

ይህ ማኅበር በአሁኑ ጊዜ ዘመናዊ በግ እርባታ የጀመረ ሲሆን በተለይ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር በጐችን ከግብርና ሚኒስቴር በማግኘትና በማዳቀል ከፍተኛ እርባታ እያካሄደ ነው በእርባታው ጣቢያ በአሁኑ ጊዜ ያለው የበጐች ብዛት ፪፻፴፩ ሲሆን አብዛኛዎቹ የበግ እናቶች በቅርብ ጊዜ የሚወለዱ ናቸው።

### የመኳቢያ አምራቾች የሚያረቧቸው በጎች

በሌላ በኩል ደግሞ አባላቱ ጥቅም የሚያገኙበትን ዘዴ አቅደው ከበጎቹ የሚገኘውን ፀጉር በሥራ ላይ በማዋል ላይ ይገኛሉ ይኸውም ፫ አባላትን በዕደ ጥበብ አሠልጥነው የሥጋጃ ሥራ እየተከናወነ ሲሆን የሥጋጃው አሠራር በተለያየ መልክ በመሆኑ ገበሬው ከፍተኛ የሥራ ውጤት በማሳየት ላይ ይገኛል ገበሬው የሥራ ውጤት በማሳየት ላይ ቢሆንም ውጤቱ ተቀባይ እንዲኖረው ያስፈልጋል ፤ ይህ ካልሆነ ግን ሠርቶ መና ስለሚቀር ገበሬው የፈጠራ ችሎታውን ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሻሻለ እንዲሄድ ለማድረግ የሥራውን ውጤት ለኅብረተሰቡ የሚያስተዋውቅ ክፍል መኖር እንዳለበት በዚህ አጋጣሚ ለመጠቆም እንወዳለን ።

የማኅበሩ ሊቀ መንበር እንዳስረዱት ማኅበራቸው በአሁኑ ወቅት ጠንካራ ጐን ያለው ቢሆንም የሥራውን ውጤት የሚወስድ ባለመኖሩ ሠራተኞቹ ይህንን ምርት ከማምረት ይልቅ ወደ እርሻው ክፍል ለጊዜው ገብተው እንዲሠሩ አድርገናቸዋል ብለዋል ።

በሌላ በኩል የአባላቱ ቤተ ሰብ በሕክምና በኩል ችግር እንዳይኖርባቸው አንዱን አባል ከውስጣቸው መርጠው ወደ ደብረ ታቦር ጤና ጥበቃ ጣቢያ ልከው እንዲሠለጥን አድርገው ባለሞያው ከሠለጠነ በኋላ አንድ ክሊኒክ ሠርተው በአሁኑ ጊዜ እያንዳንዱ አባል ያለምንም ችግር ሕክምና እያገኘ መሆኑ ታውቋል ።

በጎንደር ክፍለ ሀ/በደብረ ታቦር አውራጃ እስቴ ወረዳ የሚገኘው የዙገራ ገበሬዎች አምራቾች ኅብረት ሥራ ማኅበር ከፍተኛ የሥራ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛል ማኅበሩ ነሐሴ ፳፯ ቀን ፲፱፻፸፩ ዓ.ም ሲመሠረት የአባላቱ ብዛት ፵፫ እንደነበሩና በአሁኑ ወቅት ግን ወደ ፩፻፳ ከፍ ብለዋል ። ይህ ማኅበር ሲመሠረት በአካባቢው ያሉ አንዳንድ ሀብታም ገበሬዎች ማኅበሩ ጥንካሬ እንዳይኖረውና አባላት በአምራችነት እምነት እንዳይኖራቸው ያመረታችሁት ምርት ገቢነቱ ለመንግሥት ነው በማለት አድኃሪ ቅስቀሳውን በሰፊው ተያይዘውት እንደነበር ታውቋል ።

በሌላ በኩል ደግሞ ማኅበሩ ጨርሶ ህልውናውን እንዲያጣ ሙከራ ተደርጎ ነበር ፤ ነገር ግን የአመራር አካላት በድርጊቱ ሳይወናበዱና ሳይደናገጡ ከግብርና ሚኒስቴር ሠራተኞች ጋር ትግላቸውን በመቀጠል ይህ ማኅበር በአሁኑ ጊዜ ከፍተኛ የሆነ የምርት ውጤት በማሳየት ላይ ይገኛል በማለት የማኅበሩ ም/ሊቀ መንበር ጓድ ለውጤ አሰሙ ገልጸዋል ።

የማኅበሩ ክልል ፩፻ ፺፪ ሄክታር ሲሆን ለእርሻ ፪፻፸፩ ነጥብ ፭ ሄክታር ለደን ፸፪ ነጥብ ፱ ሄክታር ለግጦሽ ፺፫ ነጥብ ፮ ሄክታር ከፋፍሎ ለመጠቀም የተለያዩ ሰብሎችን ጤፍ ፤ ገብስ ፤ ባቄላ ፤ ዘንጋዳ ፤ ኑግ የመሳሰሉትን ያመርታል ፤ የእርሻ በሬዎች ፩፻፵ ፤ ምርጥ የወተት ላሞች ፱ እንዳሏቸው ሲታወቅ ዘመናዊ የከብትና የንብ ዕርባታም ተጀምሯል እንዲሁም በ፲፪ ነጥብ ፭ ሄክታር መሬት ላይ እንደ ድንች ሽንኩርት ፤ ጐመን ቀይ ሥርና ካሮት የመሳሰሉት እየለሙ ናቸው ።

የማኅበሩ ም/ሊቀ መንበር እንደገለጡት ካለፈው የምርት ዘመን በዚህ ዓመት ምርታችን በጣም ዝቅ ብሎ የሚገኘው በዝናም እጥረትና በፀረ ሰብል ተባዮች በመጐዳቱ ነው ሲሉ አስረድተዋል

አባላት የ፲፱፻፸፩/፸፪ የምርት ዘመን ምርታቸውን የተከፋፈሉት ባገኙት የ



www.ethiopianorthodox.org

ሥራ ነጥብ ሲሆን ከፍተኛ ነጥብ ያገኘው ብር ፷፻፹፮ ከ ፭፰ ሣንቲም መካከለኛ ነጥብ ያገኘው ብር ፷፻፹፰ ከ፳፰ ሣንቲም ሲሆን ዝቅተኛ ደረጃ ያገኘው ደግሞ ብር ፷፻፶፫ ከ፶፱ ሣንቲም መሆኑ ታውቋል ።

ይኸው ማኅበር እስከ ፬ኛ ክፍል ድረስ ያለው ት/ቤት አሠርቶ በአሁኑ ወቅት የአባላቱ ልጆች በመማር ላይ ይገኛሉ የሚያስተምሩትን ሁለት መምህራን የቀጠረለትም መንግሥት ነው አባላቱም በትርፍ ጊዜያቸው መሠረተ ትምህርት ይማራሉ ።

በተጨማሪም አባላቱ አምስት ክፍል ቤት ሠርተው ለመምህራን መኖሪያ ለግብርና ሚኒስቴር አደራጆች ቤት እንዳይቸግራቸው ያዘጋጁ ሲሆን እንዲሁም ደግሞ አንድ መጋዘን ሠርተው በሥራ ላይ አውለዋል ።

በዛሬው ጽሑፋችን ስለ እንስሳት ዕርባታና ስለ ገበሬዎች ኅብረት ተመልክተናል አንድነት ኃይል ነው እንደሚባለው በኅብረት ሠርቶ በኅብረት መጠቀም በቅዱስ መጽሐፍ የሚደገፍ ነው ከእናንተ የደከመ ሰው ቢኖር አበርቱት እንደተባለው አብሮ በመሥራት የደከመውን ለማበረታታት የሰነፈውን ለማትጋት ይቻላል አንድ በሬ ብቻውን ተጠምዶ ሊታረስ እንደማይችል በግለኝነት የሚፈጸምም ሥራ ውጤቱ ሊያስደስት አይችልምና ሁሉም ሰው የግል ብልጽግናን ከመሻት በጐንደር ክፍለ ሀገር በጋይንትና በደብረ ታቦር አውራጃ እንደተጠቀሱት ገበሬዎች አብሮ በኅብረት ሠርቶ በኅብረት ለመበልጸግ መጣር ብልህነት ነው ።

ከዚህም ጋር ምርጥ ከብቶችን ማርባት የጓሮ አትክልቶችን ማስፋፋት ውሃዎችን እየገደቡ መጠቀም የማንኛውም ሕዝብ ተግባር ሊሆን የሚገባ ነው ይህንን በግብርና ዜና የሰፈረውን አሳብ አልፈን አልፈን በመጥቀስ በመጽሔታችን የምናቀርበው አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ለመጠቀም እንዲችሉ ትምህርት ለመስጠት ነው ።

በእርግጥ አንዳንዶች ካህናት እየቀደሱ ያርሳሉ እያረሱ ይቀድሳሉ እንደነዚህ ያሉት ካህናት የልማትንና የእርሻን ሥራ ያስተምራሉ እንጂ አይማሩም ነገር ግን አንዳንድ ካህናት የግብርና ሞያ ለገበሬዎች እንጂ ለካህናትም መሆኑን ያልተረዱ ከተማ ወለዶች ሊኖሩ ይችላሉናይህንን አንብበው ትምህርት እንዲወስዱ መንፈሳዊ ጥሪያችን ይድረሳቸው ።

ፍሥሐ ባንተ

# ልብሰ ክህናት

"ወንበር በከታቡ መነኩሴ በቆቡ" እንደሚባለው ለሁሉም የተለየ ምልክት አለው ለገበሬዎች ኮፍያ ለወታደሮች መለዮ እንዳላቸው ለመነኮሳት ቆብ ለካህናት መጠምጠሚያ ሻሽ አላቸው ።

በዚህ ጽሑፍ ለመግለጽ የፈለግነው ስለካህናት ልብስና ስለመነኮሳት ቆብና ልብስ ነው ። ካህናትም ሆኑ መነኮሳት ሊታወቁ የሚችሉት በመጀመሪያ ደረጃ በልብሳቸው ነው ። ካህናት ሥልጣነ ክህነታቸው መነኮሳት መዓርገ ምንኩስናቸው ሊከበርና የሚያስተምሩትም ቃለ እግዚአብሔር ተሰምቶ በሰማዕያኑ ልቡና ሊሠርጽ የሚችለው በመጀመሪያ አለባበሳቸው የካህናትን አሠረ ፍኖት የተከተለ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ነው ።

ሐዋርያው ጳውሎስ እንደተናገረው መነኮሳትም ሆኑ ቀሳውስት ዲያቆናትም ሆነ መዘምራን በአለባበሳቸውና በሥነ ምግባራቸው ቤተ ክርስቲያንን የሚያስመሰግኑ እንጂ የሚያስነቅፉና የሚያስነውሩ ሆነው መገኘት አይገባቸውም ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ በ1950 ዓ.ም ተወያይቶ አንድ መመሪያ አውጥቷል ። መመሪያውም ስለ ካህናት ልብስ ልዩነት በሚል ርእስ ይጀምርና የመነኮሳትና የቀሳውስት የመዘምራን ልብስ ልዩ ሊሆን ይገባል ። መነኮሳት ከቆብ በላይ ሻሽ እንዳይጠመጥሙ ያልተማሩ ወንድና ሴት መነኮሳትና የሚደፉት ቆብ ስፌቱ አነስተኛ ሆኖ በራሳቸው ልክ አጭር ሊሆን ይገባል ሥልጣነ ክህነት ያላቸውና የተማሩ መነኮሳት ቆብ ደግሞ የስፌቱ ጣራ ሰብሰብ ያለ ሆኖ ጫፉ የተደፈነ እንዲሆንና በቁመቱና በስፌቱም ካልተማሩ መነኮሳት የተለየ ሊሆን ይገባል " በማለት የቆቡን ዓይነት በሥዕል ገልጾ ያሳያል ።

ቀሳውስትም በራሳቸው ላይ የሚያደርጉት ምልክት ከካርቱን የተሠራ ሆኖ ጫፉ ጨርሶ ሳይደፈን ለምልክት ያህል ክፍት ሊኖረው ይገባል ይላል ። ስለልብስም ሁኔታ ሲያብራራ ሥልጣነ ክህነት ያላቸው የተማሩ መነኮሳት በውስጥ ገበር ያለው እጀ ሰፊ ቀሚስ ሆኖ ከላይ ክብ ካባ እንዲደርቡ ተወስኖአል የልብሱ ዓይነት ግን እንደተገኘ ሊለብሱ ይችላሉ ። የቀሳውስትም ልብስ እንዲሁ እንደ መነኮሳቱ የልብስ ዓይነት ሊሆን ይገባል ። የመዘምራንና የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ልብስም ቤተ ክርስቲያንን በሚያገለግሉበት ጊዜ ከምእመናኑ የተለየ ሊሆን ይገባል በማለት ቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔውን አስተላልፏል ።

፲፱፻፶ ዓ.ም. ፪ኛ ሲኖዶስ ገጽ ፳፩-፳፫

ይህ ቅዱስ ሲኖዶስ ያወጣው መመሪያ እጅግ በጣም አስፈላጊና ጠቃሚ ነው ። መመሪያው በአንዳንድ ካህናት ዘንድ በሥራ ላይ ሲውል በአንዳንዶች ሰዎች ደግሞ በሥራ አልተተረጐመም የወጣውን መመሪያ ካለማክበር የተነሣ አንዳንድ መነኮሳት ቀሳውስትና ዲያቆናት በአለባበሳቸውም ሆነ በሥነ ምግባራቸው ከሕዝበ ክርስቲያኑ የተለየ ሁኔታ አይታይባቸውም ።

ቆባቸውም ሆነ መጠምጠሚያቸው የቅዱስ ሲኖዶስን ዓላማ የተከተለ መስሎ አይታይም የቤተ ክርስቲያናችን ሥነ ሥርዓት በሚገባ የማይጠብቁ ካህናት ራሳቸው ተዋርደው ቤተ ክርስቲያናችን የሚያዋርዱና የሚያስነቅፉ በመሆናቸው በአለባበሳቸውም ሆነ በሥነ ሥርዓታቸው ቅዱስ ሲኖዶስ ያወጣውን መመሪያ መከተል ይኖርባቸዋል ።

ቅዱስ፡ሲኖዶስ የሚያወጣውን መመሪያ ተከትለው የሚራመዱ ካህናት ራሳቸው ተከብረው ቤተ ክርስቲያኗንም ስለሚያስከብሩ በአለባበሳቸውም ሆነ በሥነ ሥርዓታቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ያወጣውንና የሚያወጣውን መመሪያ ይከተሉ እንላለን ።

ስለ ካህናት ልብስ ልዩነትና ሊያደርጉት ስለሚገባቸው የአለባበስ ሥነ ሥርዓት በሰፊው ለመረዳት እትም ፪ኛ ሲኖዶስ ገጽ ፳፩ ይመልከቱ ።

ቅ/ ሲኖዶስ ጽ/ቤት



# የጤና ዓምድ

## የወባ በሽታ

የወባ በሽታ ቆላና ወይና ደጋ በሆኑ ሥፍራዎች ከሁለት ሺ ሜትር በታች በሆኑ ዝቅተኛ አካባቢዎች የሚገኝ በሽታ ነው ።

በሽታው በጣም ረቂቅ በሆኑ ፕላስሞዲያ እነሱም

—ፕላስሞዲያ ፋልሲፓሩም

—ፕላስሞዲያ ቫይቫክስ

—ፕላስሞዲያ ማለሪያ

— ፕላስሞዲያ ኦባሊ በሚባሉ የደም ጥገኛ ሕዋሳት ምክንያት ቢምብ በተባለችው ትንኝ አስተላላፊነት የሚመጣ ለሕይወት አስጊ የሆነ አደገኛ ተላላፊ በሽታ ነው ።

<u>የወባ በሽታ መንሥኤ</u>

ለወባ በሽታ መንሥኤ ምክንያት የሚሆኑት በጣም ረቂቅ የሆኑት የወባ ሕዋሳት (ፕላስሞዲየም) በደም ሥር ገብተው በመላው ሰውነት ውስጥ ሲሠራጩ በደም ሕዋሳት ወይንም በደም ሴሎች ላይ ጉዳት በማድረስ በተለከፈው ሰው ላይ ከፍ ያለ የጤንነት መታወክ ያስከትላል ።

የወባ በሽታ ምልክቶች

በሽታው ሲይዝ በድንገት ወይንም ቀስ በቀስ ይጀምራል መጀመሪያ ሲጀምር ሁኔታው ግልጽ ሆኖ በማይለይ መታወክ ሁኔታ ይጀምራል ከዚያም ቀጥሎ ያሉት ምልክቶች ይከሰታሉ ። የሰውነት መቀረጣጠፍ ብርድ ብርድ ማለት ማንቀጥቀጥ ራስ ምታት ከፍተኛ ትኩሳት በላብ መዘፈቅ ምግብ ማስጠላት ማቅለሽለሽ ሃሞት ማስታወክ የደም ማነስ (መገርጣት አኑሚያ) የጣፊያ አንዳንዴም የጉበት ማበጥ ናቸው ። የራስ ምታቱ የትኩሳቱ የብርድ ብርድ ማለቱና በላብ የመዘፈቁ ምልክቶች አጠር ላለ ጊዜ ይጠፉና በሽተኛው የተሻለው ይመስላል ሆኖም እንደየሕዋሳቱ ዓይነት በየቀኑ ወይም በየሁለት ቀኑ አለዚያም በየሶስት ደግሞ በየአራት ቀኑ እያገረሹ ሕመምተኛውን እጅግ በጣም ያሰቃያሉ።

የወባ በሽታ እንዴት እንደሚተላለፍ

በሽታውን የምታስተላልፈው እንስቲቷ ትንኝ ምግቧ የሰው ደም ነው ትንኟ ከጥቂት ጊዜ በኋላ እንደገና ደም ለመጠጣት ከሰው ወደ ሰው ትዘዋወራለች ።

ጤናማ የሆነውን ሰው አግኝታ ከነከሰች ቀደም ሲል በወባ ከታመመው ሰው ደም ጋር ጠጥታቸው የነበረውን የወባ በሽታ ሕዋሳት ከምራቋ ጋር በዚህ በጤናማው ሰው የደም ሥር እንዲገቡ ታደርጋለች ሕዋሳቱም በደም ሥሩ በኩል አድርገው በመላው ሰውነቱ ይሠራጫሉ ይህ ከሆነ ከጥቂት ቀኖች በኋላ ሰውዬው በጠና ይታመማል ይህ ሰው በሌላ ትንኝ ቢነከስና የነከሰችው ትንኝ ሌላ ጤናማ ሰው ብትነክስ ጤናማው ሰው በወባ በሽታ ይያዛል ። በዚህ ሁኔታ የወባ በሽታ በትንኝ አማካይነት ከሰው ወደ ሰው ይዛመታል ። በተለይም ደግሞ ሕፃናት በወባ በሽታ የተያዙ ወይንም የተለከፉ እንደሆነ ሁኔታው እጅግ አስከፊና አሰቃቂ ሊሆን ይችላል ።

**የወባን በሽታ እንዴት መከላከል ይቻላል** የወባ በሽታ የኅብረተሰብ በሽታ ስለሆነ ይህንኑ በሽታ ለመከላከል ለሚደረገው ጥረት ሁሉ ኅብረተሰቡ የመተባበር ግዴታ አለበት ይኸውም፡-

— <u>የወባ ትንኞች የሚራቡበትን ቦታ ማጥፋት</u>

— ትንኙን በመድኃኒት ማጥፋት ነው መድኃኒት ስንል እንደ ዲዲቲ ወይም ሌሎችን መድኃኒቶች ነው

— አንድ ሰው በወባ በሽታ ከተያዘ በአስቸኳይ ተመርምሮ የሚያስፈልገውን ሕክምና ማድረግና ከበሽታው ሕዋሳት ነፃ መሆን አለበት ይህ ካልተደረገ ከላይ እንደተጠቀሰው ከሞት አደጋ ሊያደርስ ይችላል ።

— የወባ በሽታ ከሚገኙባቸው ሥፍራዎች በአጭር ጊዜ የሚኖር ሰው በ… ሣምንቱ የወባ መከላከያ መድኃኒት መውሰድ ግዴታ ነው ።

ክ/ሲ የሺወርቅ ከቦ…



www.ethiopianorthodox.org

# የአለን ቅዱስ ጊዮርጊስ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ተፈጸመ

በከፋ ሀገረ ስብከት በጅማ ከተማ የሚገኘው የአለን ቅዱስ ጊዮርጊስ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ሥራ ተፈጽሞ ሚያዝያ ፳፫ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ.ም ቅዳሴ ቤቱ ተከብሯል ። በበዓሉም ላይ የከፋ ሀ/ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ጢሞቴዎስ ተገኝተው አዲስ የተሠራውን ቤተ ክርስቲያን በመባረክ ታቦቱ ወደ አዲሱ ቤተ መቅደስ እንዲገባ አድርገዋል ።

ሚያዝያ ፳፫ ቀን በየዓመቱ የሚከበረውን የቅዱስ ጊዮርጊስን በዓለ ንግሥና የሕንፃ ቤተ ክርስቲያኑን ምረቃ በዓል ለማክበር በጅማ ከተማ የሚገኙ ካህናትና በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ምእመናን ተገኝተዋል ።

በዚህም ታላቅ በዓል ምክንያት ለተሰበሰቡት ምእመናን ብፁዕ አቡነ ጢሞቴዎስ የከፋ ሀ/ስብከት ሊቀ ጳጳስ መንፈሳዊ መልእክትን አስተላልፈዋል። ብፁዕነታቸው የሰማዕቱን ቅዱስ ጊዮርጊስ ተጋድሎና ስለ ክርስቶስ ፍቅር የተቀበላቸውን ፀዋትወ መከራ አንድ በአንድ ዘርዝረው ከተናገሩ በኋላ ቅዱስ ጊዮርጊስ ከሀብታም ቤተሰብ የተገኘ ሆኖ ሳለ ሀብትን በመውደድ በክብርና በብልጽግና ለመኖር አልፈለገም ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ልትሆን ብትወድ ሂድና ያለህን ሁሉ ሸጠህ ለድሆች ስጥ መዝገብም በሰማያት ታገኛለህ መጥተህም ተከተለኝ ያለውን ቃል በማሰብ ከወላጆቹ ያገኘውን ገንዘብ ሁሉ ለችግረኞች ሰጥቶ ከጨረሰ በኋላ በሰው ፊት የሚመሰክርልኝ እኔም በሰማያዊ አባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ ያለውን አምላካዊ ቃል መሠረት በማድረግ በአላውያን ነገሥታት ፊት ስለሃይማኖቱ ታግሎ ድል በማድረጉ የሰማዕትነት የክብር አክሊልን መቀዳጀቱን ገልጸዋል ።

ቀጥሎም ብፁዕነታቸው ስለ ቤተ ክርስቲያኑ ሕንፃ ባደረጉት ገለጻ ላይ ይህ አሁን አምሮና አሸብርቆ የሚታየው ቤተ ክርስቲያን ከመጐዳቱ የተነሣ ሕንፃው ተንዶ በሰው ሕይወት ላይ አደጋ ያደርሳል እየተባለ ይፈራ ነበር ዛሬ ግን በምእመናኑ ጥረት ታድሶ ስንመለከተው እጅግ በጣም ያስደስተናል ብለዋል በተጨማሪም በጉልበታቸውም በገንዘባቸውም ትብብር ያደረጉትን አመስግነው ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ



የአለን ቅ ዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን

ሃይማኖት የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ለዚሁ ቤተ ክርስቲያን ሕንፃ ማሠሪያ ብር ፫.ሺ. በመርዳታቸው በራሳቸውና በምእመናኑ ስም ለቅዱስነታቸው ምስጋና ካቀረቡ በኋላ ጸሎተ ቡራኬ በማድረግ የበዓሉ ፍጻሜ ሆኖአል ።

ከብፁዕ አቡነ ጢሞቴዎስ ትምህርት በፊት የቤተ ክርስቲያኑ ሕንፃ አሠሪ ኮሚቴ ያዘጋጀው ሪፖርት በኮሚቴው ሊቀ መንበር ባላምባራስ አድማሱ ጥሩነህ በንባብ ተሰምቷል ። ከቀረበው ሪፖርት ለመረዳት እንደተቻለው ይህ ቤተ ክርስቲያን ቀደም ሲል የተሠራው በቤተ ክርስቲያን ፎርም ሳይሆን በሌላ ቢሆንም በእርጅና ምክንያት የፈረሰ በመሆኑ የካቲት ፯ ቀን ፲፱፻፸፬ ዓ.ም. ስብሰባ ተደርጐ ውይይት ከተካሄደ በኋላ አሠሪ ኮሚቴ ተመርጦ ከኮሚቴው ትጋት ጋር ምእመናኑም ስለተባበሩ የቤተ ክርስቲያኑ ሥራ ተፈጽሞ ሁላችንም ለማየት በቅተናል ይህንንም ሥራ ላስፈጸመን ቸር አምላካችን ክብርና ምስጋና ልናቀርብለት ይገባናል ብለዋል የኮሚቴው ሊቀ መንበር ለዚሁ ቤተ ክርስቲያን ርዳታ ያደረጉትን እንደሚከተለው በመዘርዘር ተናግረዋል ።

| | | |
|---|---|---|
| ፩ኛ/ | ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለሃይማኖት የኢትዮጵያ ፓትርያርክ | ብር፫ሺ. |
| ፪ኛ/ | አቶ ጌታቸው ወልደ ማርያም | ፩ሺ.፰፻ |
| ፫ኛ/ | ወ/ሮ አስካለ አሊ ብር | ፩ሺ.፫፻ |
| ፬ኛ/ | አቶ ልንገርህ ቸኮል | ፩ሺ.ህ |
| ፭ኛ/ | አበራሽ ተሰማ | ፭፻፹ |
| ፮ኛ/ | አቶ አህመድ መሀመድ | ፫፻፤ ፭፻ |
| ፯ኛ/ | አቶ ግዛቸው ተከሉ | ፭፻ |

ወደ ገጽ ፩ ዞሯል



# ኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ

የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ፡

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ ፡

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፡ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፡ መንፈሳዊ ዛመናዊ መዝሙሮችን ፡ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቲፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆነ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ ላላቀረቡ ግን ሰባት ብር በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት ፡

የስልክ ቍ. 11
የመልእክት ሣ. ቍ. 31
አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org